# መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ

ይህ መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ሦስት ድርብ ወይም ጣምራ መጻሕፍት አንደኛው ነው፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት፣ 1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕል፡፡ እነዚህ ሦስት ድርብ መጻሕፍት የእሥራኤልን መንግሥት መነሣትና መውደቅ የሚተርኩ ናቸው፡፡

ብሉይ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት ቋንቋ፣ ማለትም በዕብራይስጥ በተጻፈው ብሉይ ኪዳን፣ 1ኛ እና 2ኛ በመባል የተከፋፈሉት እነዚህ ሦስት ድርብ መጻሕፍት አንድ አንድ መጻሕፍት ብቻ ነበሩ፡፡ ለሁለት የተከፈሉት «ሴፕቱጀንት» (Septuagint) የተባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ከክርስቶስ ልደት 300 ዓመታት በፊት አካባቢ መጽሐፍ ቅዱስን፣ ማለትም ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ሲተረጉሙ ነው፡፡ «ሴፕቱጀንት» በግሪክ 70 ማለት ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የተርጓሚዎቹ ብዛት 70 ያህል መሆኑን ነው፡፡

እነዚህ ተርጓሚዎች፣
ከ1ኛ ሳሙኤል እስከ 2 ነገሥት ድረስ ያሉትን አራት መጻሕፍት፣ 1ኛ ሳሙኤልን 2ኛ ነገሥት በማለት እስከ 4ኛ ነገሥት ሰይመዋቸው ነበር፡፡ በ1962 የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ያመለክታል፡፡ መጽሐፈ ሳሜኤል ቀዳማዊ ካለ በኋላ በቅንፍ እርሱም መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ነው ይላል፡፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ ላይ ደግሞ በቅንፍ እርሱም መጽሐፈ ነገሥት ካልእ ነው ይላል፡፡ እንደዚህ እያለ መጽሐፈ ነገሥት ካልእን በቅንፍ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕን ራብዕ አራተኛ ይለዋል፡፡

አንደኛ ሳሙኤል፣ የመጨረሻው «መስፍን» ወይም «ፈራጅ» የሆነው ሳሙኤል ከመወለዱ ጀምሮ የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ሳዖል እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ይሄዳል፡፡ ሁለተኛ ሳሙኤል ደግሞ የዳዊትን 40 ዓመት ንግሥ ይተርካል፡፡ የአንደኛ ሳሙኤል ዋና መልእክት እስራኤላውያን እግዚአብሔር ራሱ ከሚያስተዳድረው ሕዝብ (Theocracy) ሰው ወደሚያስተዳድረው ሕዝብ Monarchy ሥርዓት እንደሄዱና ይህም ምርጫቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን የእነርሱ ፈቃድ እንደነበረ እናያለን፡፡

ይህ መጽሐፍ በሦስት ግለሰቦች ታሪክ የተሞላ ነው፡፡ እነዚህም ግለሰቦች ሳሙኤል፣ ሳዖልና ዳዊት ሲሆኑ በመጽሐፉም የሚከፋፍለው በእነዚህ ሦስት ግለሰቦች ላይ ነው፡፡

## ሳሙኤል፡- የመጨረሻው ፈራጅ (መስፍን) ከምዕራፍ 1-7

- ልደቱና እድገቱ (ምዕ. 1-2)
- ጥሪው (ምዕ 3)
- አገልግሎቱ (ምዕ 4-7)

## ሳዖል፡- የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ (ከምዕ. 8-15)

- የሳዖል መንገስ (ከምዕ. 8-10)
- መልካም ጅማሬ (ከምዕ. 11-12)

- የሳዖል ውድቀት ከምዕ. 13-15)

## ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ንጉሥ

ከምዕ. (16-31)

- መቀባቱ (ምዕ. 16÷1-13)
- ሳዖልን ማገልገሉ (ምዕ 16÷14-18፡5)
- በሳዖል መሰደዱ (ምዕ. 18፡6 ምዕ. 31)

አከፋፈሉ እንደዚህ ቢሆንም የአንዱ ታሪክ በሌላው ክፍል የለም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን የዚያ ክፍል ዋና ትኩረት ማን ላይ እንደሆነ የሚያመለክት አከፋፈል ነው።

በዚህ መጽሐፍ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ ውስጥ ምን ያህል ታላቅ ሚና እንደተጫወተ እናያለን።

- የመጨረሻው ፈራጅና መስፍን ነበረ
- የነቢያትን ጉባኤ (Schools of the prophets) ጀመረ
- የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ንጉሥ ቀባ

በሐዋ. 3÷24 መልክ ባለው መንገድ የነቢያት አገልግሎት የተጀመረው ከሳሙኤል ጀምሮ እንደሆነ እናያለን።

«<u>ከሳሙኤል ጀምሮ</u> ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነቢያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ።»

ምንም እንኳን ከሳሙኤል በፊት ሙሴ ነቢይ ተብሎ ቢጠራም የነቢያት አገልግሎት ጀማሪ ሆኖ የሚታየው ሳሙኤል ነው።

በሉቃስ 16÷31 አብርሃም ለዚያ ሀብታም ሰው «ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።»

በዚህ ጥቅስ ሙሴን ከነቢያት ለይቶ ይጠቅሰዋል የሙሴ ዋና ትኩረት በሕግ ላይ እንጂ በነቢይነቱ ላይ አልነበረም። ሳሙኤል ግን የነቢያትን ጉባኤና ትምህርት ቤት የጀመረ ነው።

በሐዋ 13÷20 ላይ ደግሞ «ከዚህም በኋላ እስከ ነቢዩ እስከ ሳሙኤል ድረስ አራት መቶ አምሳ ዓመት ያህል መሳፍንትን ሰጣቸው። የሚል ቃል እናገኛለን።

1ኛ ሳሙኤልን እስከ ምዕራፍ 24 ድረስ ሳሙኤል ራሱ እንደጻፈ ሲታመን። ከምዕ. 25፤ የሳሙኤልን ሞት ከሚያወሳው ምዕራፍ ጀምሮ እስከ 2ኛ ሳሙኤል መጨረሻ ድረስ ነቢዩ ናታንና ጋድ እንደጻፉት ይገመታል። ይህንን የሚያመለክት ቃል በ1ኛ ዜና መዋዕል 29÷29 እናነባለን። «የንጉሡም የዳዊት የፊተኛውና የኋለኛው ነገር እነሆ በባለ ራእዩ በሳሙኤል ታሪክ በነቢዩም በናታን ታሪክ። በባለራዕዩም በጋድ ታሪክ ተጽፏል።»

ክፍል አንድ፤ ሳሙኤል ምዕ. 1-7

## ምዕራፍ አንድ

የሳሙኤል አባት ሕልቃና እና የእናቱን የሐናን አጭር ታሪክ የያዘ ሲሆን ሳሙኤል በምን ዓይነት በጭንቅና በጽኑ ጸሎት እንደተወለደ ያሳየናል። ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ እግዚአብሔር አንድ ልዩ ነገርን በሕይወታችን ማድረግ (መውለድ) ሲፈልግ፣ ሊያከብረን ሲፈልግ፣ መጀመሪያ በምንማረርበት፣ በምንጨነቅበትና በምናለቅስበት መንገድ እንደሚመራን ነው። እግዚአብሔር መዋረድን ሳናውቅ መክበርን፤ ማጣትን ሳናውቅ ማግኘትን እንድናውቅ ስለማይፈልግ መጀመሪያ በእኛ ሊወለድ ላለው ነገር ያዘጋጀናል። ይህንንም የሚያደርገው፣ ነገሩ ከእኛ ሳይሆን ከእርሱ እንደሆነ እንድናውቅና ለእርሱ ክብር ብቻ እንድናደርገው ስለሚፈልግ ነው።

ቁ. 10 «እርስዋም (ሐና) በልብዋ ትመረር ነበር በእግዚአብሔርም ፊት ጸለየች <u>ጽኑ ልቅሶም አለቀሰች</u>።»

የሐና ጸሎት፤ <u>ጾምና ስእለት</u> የተጨመረበት ልመና እንደነበረ እናያለን። እነዚህ ሁለት ነገሮች በተለይ አንድ ከባድ ነገር ስንለምን፤ የልመና ጸሎታችንን የበለጠ ያጠነክራሉ።

በዚሁ ምዕራፍ፤ በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህን የነበረውን ነገር ግን በመንፈሳዊ ህይወቱ ደንዝዞ የነበረውን ዔሊን እናያለን።
12-13 «ጸሎትዋንም በእግዚአብሔር ፊት ባበዛች ጊዜ ዔሊ <u>አፍዋን</u> ይመለከት ነበር ... ዔሊም እንደ ሰከረች ቆጠራት።» የእግዚአብሔር ሰዎች ከልብ ይልቅ አፍን (ውጫዊውን ብቻ) መመልከት ሲጀምሩ ደንዝዘዋል ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን «እኛ ግን የክርስቶስ ልብ (ወይም አእምሮ) አለን» ነው የሚለው።

## ምዕራፍ ሁለት

በዚህ ምዕራፍ፣ ሐና በስእለት ያገኘችውን ልጅ ለእግዚአብሔር ከሰጠች በኋላ ያቀረበችውን ጸሎት ከቁ. 1-10 ስናነብ ከቁ. 11-37 ደግሞ በዚያ ጊዜ ሊቀካህን ስለነበረው ስለ ዔሊና ስለ ልጆቹ የሚናገር ክፍል ነው።

ቁ. 1 «... ልቤ በእግዚአብሔር ጸና

ቀንዶ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ

አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ። »

ልባችን መጽናት ያለበት በእግዚአብሔር እንጂ በሌላ በምንም ነገር መሆን የለበትም፤ በዕብ 13፥9 «ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም» ይለናል። እንዲሁም ቀንዳችን (ኃይላችን) በእግዚአብሔር እንጂ በሌላ ነገር ከፍ ከፍ ማለት የለበትም። ዘማሪው በመዝሙረ ዳዊት «ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው» በማለት መስክሮአል። ኤፌ. 6፥10

«በቀረውስ፣ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።» ይለናል።

ከቁ. 11-37 የሳሙኤልን ከብላቴንነቱ ጀምሮ እግዚአብሔርን ማገልገል፤ ካህናት የነበሩት የዔሊ ልጆች ግን የእግዚአብሔርን ቁርባን በመናቅ እግዚአብሔርን እንዳስቆጡና ከእግዚአብሔር ዘንድ ለዔሊ የመጣለትን ተግሣጽ እናነባለን።

ቁ. 11, 21, 26, «ብላቴናውም ሳሙኤል በካህኑ በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። ... ብላቴናውም (ሳሙኤል) በእግዚአብሔር ፊት አደገ ... ብላቴናውም ሳሙኤል እያደገ ሄደ በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ሞገስ እያገኘ ሄደ።»

ስለ ዔሊ ልጆች ግን፤
ቁ. 12 እና 17 «የዔሊም ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ ... ሰዎቹም የእግዚአብሔርን ቁርባን ይንቁ ነበርና የጐበዛዝቱ ኀጢአት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ታላቅ ነበረች» ይላል።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለዔሊ መልእክት ይልካል፤ ቁ. 29-30 «... ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርህ? .. ያከበሩኝን አከብራለሁና የናቁኝም ይናቃሉና» በማለት በእርሱና በልጆቹ እንዲሁም በዘሩ ሁሉ ሊደርስበት ያለውን እርግማን ይነግረዋል።

በቁ. 27 ላይ «የእግዚአብሔርም ሰው ወደ ዔሊ መጥቶ አለው፡ -» የሚል ቃል እናነባለን። ይህ የእግዚአብሔር ሰው ማን እንደሆነ እንኳን በስም አልተገለጸም። በዚያ ዘመን ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ እንደነበረ በም 3÷1 ላይ እናያለን። ከዚህ ስሙ ካልተጠቀሰ የእግዚአብሔር ሰው የምንማረው፤ የእግዚአብሔር ድምፅን የሚሰሙና የሚያስተላልፉ ድብቅ ሰዎች እንዳሉት ነው። በመጨረሻም እግዚአብሔር በዚህ ሰው ለዔሊ እንዲህ ይለዋል፤

ቁ. 35 «የታመነም ካህን ለእኔ አስነሣለሁ፤ በልቤም በነፍሴም እንዳለ እንዲሁ ያደርጋል፤ እኔም የታመነ ቤት እሠራለታለሁ፣ ዘመኑን ሁሉ እኔ በቀባሁት ሰው ፊት ይሄዳል።» ከዚህ ጥቅስ የምንማረው፤ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ካህን ወይም አገልጋይ የሚያደርገው በእግዚአብሔር ልብና ነፍስ ያለውን እንጂ በራሱ ልብ ያለውን የራሱን ሐሳብ ወይም የሌሎችን ሐሳብ አይደለም። ስለ ዳዊት የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው፤ ሐዋ. 13÷36 «ዳዊትም በራሱ ዘመን <u>የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ</u>።»

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

<u>የሳሙኤል በእግዚአብሔር መጠራት</u>

ቁ. 1ሀ. «ብላቴናው ያገለግል የነበረው ዔሊን በማገልገል ነበረ»።

እግዚአብሔርን ያገለግል የነበረው ዔሊን በማገልገል ነበረ። የእግዚአብሔር ቃል ስለ ኤልሳዕ እንዲህ ይላል። «... ኤልያስን ተከትሎ ሄደ፣ ያገለግለውም ነበር።» 1ኛ ነገ. 19÷21

በተጨማሪም በ2ነገ 3÷11 ላይ ኤልሳዕ የኤልያስ እጅ አስታጣቢ እንደነበረ ይናገራል፤ «... በኤልያስ እጅ ውሃ ያፈስስ የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ» ይለዋል።

ቁ. 1ለ «የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበር።» የእግዚአብሔር ሰዎች ፈዝዘውና ደንዝዘው ቃልን ከእግዚአብሔር በማይቀበሉበት ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ይሆናል። የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ምክንያት ይጠፋል።

ቁ. 3-4 «ሳሙኤልም የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በእግዚብሔር መቅደስ ተኝቶ ሳለ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው» የእግዚአብሔር ድምፅ ወደ እኛ የሚመጣው የእግዚአብሔር ክብር ባለበት በቅድስና ስፍራ ስንሆን ነው።

ቁ. 7 «ሳሙኤል ግን ገና እግዚአብሔርን አላወቀም ነበር፤ የእግዚአብሔርም ቃል ገና አልተገለጠበትም ነበር።» ሳሙኤል ገና ብላቴና ስለነበረ እግዚአብሔርን ገና ባያውቅም <u>አገልግሎት በመሠረቱ የመታዘዝ ጉዳይ</u> ስለነበረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያገለግል ነበር።

ቁ. 9 «ዔሊም ሳሙኤልን፡ - ሄደህ ተኛ ቢጠራህም፡ - አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው አለው።»
ዔሊ ምንም የፈዘዘበትና የደነዘዘበት ዘመን ቢሆንም ሳሙኤል በትህትና ከእርሱ ይማር ነበር። ዔሊ ግን ራሱ የማያደርገውን ነገር ነበረ ለሳሙኤል የሚመክረው። የራሱ ጆሮዎች ለእግዚአብሔር ቃል ደንዝዘው ነበር።

ቁ. 13 «ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውምና ...»
ልጆችን ማረምና ከእርግማን መጠበቅ የወላጆች በተለይም የአባቶች ኃላፊነት እንደሆነ ያስተምረናል።

ቁ. 18 «ዔሊም፡ - እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ ደስ ያሰኘውን ያድርግ አለ።»
እግዚአብሔር ሲገሥጸን፡ -

1. በንስሐ መውደቅና ምሕረትን መቀበል
2. ለምን ተገሠጽኩ ብሎ ማማረር፣ ማጉረምረም ወይም ተስፋ መቁረጥ እና መድከም (ዕብ. 12÷5-6)
3. እንደ ዔሊ በግዴለሽነት ነገሩን ማየት እንችላለን።

የዔሊ ቃል ለእግዚአብሔር የመገዛት ቃል ሲሆን የግዴየለሽነት ቃል ነበር።

ቁ. 19 «ሳሙኤልም አደገ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፣ ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር።» ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበረ፣ እግዚአብሔር ከሳሙኤል ጋር ነበረ። እግዚአብሔር ከሳሙኤል ጋር ከአንደበቱም ጋር ስለነበረ ደግሞ የሳሙኤል ቃል እንደ እግዚአብሔር ቃል ነበረ «አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር»
ማቴ 12÷36 «ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል»

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

ኢካቦድ፡ - ክብር ከእስራኤል ለቀቀ
ቁ. 2 «... እስራኤል በፍልስጥኤማውያን ፊት ተመቱ።»
እግዚአብሔር በዘዳ 23÷9 ላይ «ጠላቶችህን ልትወጋ በወጣህ ጊዜ ከክፉ ነገር ሁሉ ሰውነትህን ጠብቅ» ብሏቸው ነበር፤ ነገር ግን ይህንን ቃል ሳይታዘዙ ከካህናቱ ጀምሮ ሕዝቡም ጭምር በእግዚአብሔር ፊት ረክሰው ነበር። «... የጎበዛዝቱ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ታላቅ ነበረች።» ምዕ. 2÷17

ቁ. 3 «... የእስራኤልም ሽማግሌዎች ዛሬ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ፊት ስለምን መታን?» አሉ። ትክክለኛውን ጥያቄ ነበር የጠየቁት ምክንያቱም የመቱአቸው ፍልስጥኤማውያን ሳይሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ነበርና።
ነገር ግን፤ ለጠየቁት ትክክለኛ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ አላገኙም።

«በመካከላችን እንዲሄድ ከጠላቶቻችንም እጅ እንዲያድነን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት ከሴሎ እናምጣ አሉ።» ወደ ራሳቸው ሕይወት ተመልክተው፤ ይህ ሽንፈት የደረሰብን ከኃጢአታችን የተነሣ ነው ብለው በእግዚአብሔር ፊት በንስሐ ከመውደቅ ይልቅ ወደ ውጫዊ የሃይማኖት ሥርዓት አዘነበሉ። የእግዚአብሔር ዋነኛ ትኩረት የግል ሕይወታችን ነው እንጂ የሃይማኖት ሥርዓት አይደለም።

ቁ. 4 -7

«... አፊንና ፊንሃስ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ጋር በዚያ ነበሩ። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ እስራኤል ሁሉ ታላቅ እልልታ አደረጉ ምድሪቱም አስተጋባች ... ፍልስጥኤማውያንም ፈርተው እግዚአብሔር ወደ ሰፈር መጥቶአል አሉ።» ቅድስና የሌለው የሃይማኖት ሥርዐትና አምልኮ ታላቅ እልልታና ማስተጋባት ሊኖርበት ይችላል፤ ጠላትንም እንኳን ሊያስፈራ ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር የለበትም፤ ድልንም አይሰጥም ምናልባት አምልኮውን ይመሩ የነበሩት ሁለቱ የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ነበሩ። ሕይወታቸው ግን በእግዚአብሔር ፊት አጸያፊ ነበረ። እግዚአብሔር እንዴት በዚህ ቅድስና በሌለበት፣ ነገር ግን ብዙ ሞቅታ ባለበት አምልኮ ውስጥ ይገኛል?

ቁ. 10 «... እስራኤልም ተመቱ ... የእግዚአብሔርም ታቦት ተማረከች።»

እግዚአብሔር፤ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ ቃል ኪዳኑን ባፈረሱ እጅ እንዲሆን አልፈቀደም፤ ስለዚህም ታቦቱ ተማረከ፣ ይመኩበት የነበረው የሃይማኖት ሥርዐት ፈረሰ።

ቁ. 13 «ዔሊ ስለ እግዚአብሔር ታቦት ልቡ ተናውጦ ነበርና በመንገድ ዳር ... ይጠባበቅ ነበር» የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን፣ የእግዚአብሔርን ቃል አፍርሶ የቃል ኪዳን ምስል የሆነው ታቦት እንደ ጣዖት ሆኖበት ነበር። በኢሳ. 29፥13 «ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፣ በሰዎች ሥርዐትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና» ይላል። እግዚአብሔር፤ ልባችን በውጫዊ ሥርዓትና በታቦት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል እንዲናወጥ ነው የሚፈልገው፤

ኢሳ. 66፥1-2 «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነውን? እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል፤ እግዚአብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፣ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፣ በቃሉም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ።»

ለዔሊን የእግዚአብሔር ቃል ሁለት ጊዜ በምዕ 2ትና3 ሲመጣለት አላንቀጠቀጠውም አላናወጠ ውም። ቃሉ ከኃይለኛነቱ የተነሣ «የሰማውን ሁሉ ሁለቱ ጆሮቹ ጭው የሚያደርግ» ምዕ. 3፥11 ነበር። ነገር ግን ሁለቱ ጆሮቹ ከመደንዘዛቸው የተነሣ ይህ ኃይለኛ ቃል አላናወጠውም ነበር።

የሃይማኖት ሥርዓት ግን ልቡን ሲያናውጠው እናያለን።
«ዔሊ ስለ እግዚአብሔር ታቦት ልቡ ተናውጦ ነበር» ምዕ. 4፥13
ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ይልቅ የሃይማኖትን ሥርዓት ስናከብር ውጤቱ፤
«ዔሊ ... አንገቱ ተሰብሮ ሞተ» ቁ. 18
«ክብር ከእስራኤል ለቀቀ» ቁ. 22

ምዕ 5፥6 ብቻውን ተዓምራትን የሚያደርግ አምላክ፣ በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች እንደምናየው፤ የእግዚአብሔር ታቦት በፍልስጥኤማውያን ተማርካ ከተወሰደች በኋላ በፍልስጥኤማውያንና በአምላካቸው በዳጎን ላይ ታላቅ ሥራ ይሠራል።

በዘጸ 25፥10-22 ስለ እግዚአብሔር ታቦት አሠራርና ዓላማ በምናነብበት ጊዜ የእግዚአብሔር ታቦት ሦስት ነገሮችን እንደሚያመለክት እናያለን፤

1. የእግዚአብሔርን መገኘት /Presence/ ያመለክታል
2. የእግዚአብሔርን ክብር ያመለክታል፡- እግዚአብሔር በሚገኝበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ክብር ስላለ።
3. የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ያመለክታል።

ይህን የእግዚአብሔር መገኘት፣ ክብርና ቃል ኪዳን ያለበትን ታቦት ፍልስጥኤማውያን ወስደው በአምላካቸው በዳጎን ቤት አኖሩት። በእነርሱ ሐሳብ አምላካቸው ዳጎን ከእስራኤል አምላክ ስለሚበልጥ ድልን በእስራኤል ላይ ሰጥቷቸዋል፤ ስለዚህ የእስራኤል አምላክ ታቦት ክብርን ለዳጎን እንዲሰጥ ብለው በዳጎን ፊት አስቀመጡት። ቁ. 3 «በነጋውም የአዛጦን ሰዎች ማለዳ እነሆም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር» በእግዚአብሔር ታቦት ላይ የእግዚአብሔር ክብርና መገኘት ነበር በዳጎን ላይ ግን የሰይጣን የአጋንንት መንፈስ ነበረ። ጉልበት ሁሉ በሚንበረከክለት አምላክ ፊት በዳጎን ላይ የነበረው ርኩስ መንፈስ ሲንበረከክ የዳጎን ምስል አብሮ በታቦቱ ፊት በግምባሩ ተደፋ።

ቁ. 3ለ «ዳጎንንም አንሥተው ወደ ስፍራው መለሱት» ፍልስጥኤማውያን አምላካቸው በእስራኤል አምላክ ፊት ወድቆ ሲያዩ አምላካቸውን አንሥተው ወደ ስፍራው ይመልሱታል። ብዙ ሰዎችም በዓለም ውስጥ እነርሱ ሲወድቁ የሚያነሣቸውን አምላክ ሳይሆን፣ እየወደቀባቸው አንሥተው በስፍራው የሚመልሱትን ጣዖት ነው የሚያመልኩት። ከእነዚህ ጣዖቶች አንዳንዶቹ፤ መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ገንዘብ፣ ምድራዊ ዕውቀትና ፍልስፍና ወዘተ ናቸው። ኮሚኒዝም ለብዙ ዓመታት በአገራችን ላይ እንደ ዳጎን ሆኖ ነግሦ ነበር። እግዚአብሔር በቃሁ ሲለው ግን በግንባሩ ወድቆ ሲንኮታኮት አይተናል። አንዳንዶች ግን መልሰው ሊያቆሙት የሚሞክሩ ይኖሩ ይሆናል። እኛ ግን ስንወድቅ የሚያነሣን እንጂ ወድቆ አንሱኝ የሚለን አምላክ የለንም።

ዳጎንን አንሥተው ካስቀመጡት በኋላ፤
ቁ.4 «በነጋውም ማለዳ እነሆም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር፤ የዳጎንም ራስ እጆቹም ተቆርጠው በመድረኩ ላይ ወድቀው ነበር የዳጎንም ደረት ብቻውን ቀርቶ ነበር።»

የመጀመሪያው በግምባሩ መውደቅ ስላልበቃው ለሁለተኛ ጊዜ በግምባሩ መውደቅ ብቻ ሳይሆን ከጥቅም ውጭ ይሆናል። ቦክስ የሚጫወቱ ሰዎች ተቀናቃኞቻቸውን መትተው እንደሚዘርሩ /Knock Down/ አንዳንድ ጊዜም ከጨዋታው እንደሚያስወጡ /Knock Out/ ዳጎንም በመጀመሪያው ዙር /Knock Down/ ሲሆን፤ እናያለን። በሁለተኛው ዙር ግን /Knocked Out/ (ከጥቅም ውጭ) ሆነ። «እነሆም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር፤ <u>የዳጎንም ራስ እጆቹም</u> ተቆርጠው በመድረክ ላይ ወድቀው ነበር የዳጎንም ደረት ብቻውን ቀርቶ ነበር።» 1ሳሙ 5፥4

1. የዳጎን ራስ ተቆረጠ፤ ራስ ሥልጣንን ያመለክታል በዘፍ. 3፥15 «እርሱ ክርስቶስ <u>ራስህን</u> ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።» ሲል ክርስቶስ የሰይጣንን ራስ (ሥልጣን) እንደሚያፈርስ የሚያመለክት ነው።

2. የዳጎን እጆች ተቆረጡ፡ - እጅ ሥራን ያመለክታል።

1ዮሐ. 3÷8 «የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡»

3. የዳጎንም ደረት ብቻውን ቀርቶ ነበር ደረት ወኔን ያመለክታል፡፡ አንድ ሰው ደረቱን ገልብጦ መጣ ስንል በወኔና በትምክህት መጣ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ደረት ብቻውን ያለ ራስና እጅ ምንም ፋይዳ የለውም፡፡ ወኔ ብቻውን ያለ ሥልጣንና ያለ ሥራ ምንም ሊያደርግ አይችልም፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ የተሸነፈ በመሰለበት ሁኔታ ላይ የሰይጣንን ራስ ቀጥቅጦና ሥራውን አፍርሶ ደረቱ ብቻ እንዲቀር አድርጎታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጠላት በወኔ እና በማስፈራራት ማንነቱን የማያውቀውን አማኝ ሊያጠቃ ይችላል እንጂ ራሱና እጁ እንደ ተቆረጠ የሚያውቀውን አማኝ ምንም ሊያደርገው ሥልጣንና መብት የለውም፡፡

(በአዲሱ እትም) ቆላ 2÷15 «አለቆችንና ባለሥልጣኖችን በመስቀሉ ድል ነሥቶ ትጥቃቸውን ካስፈታ በኋላ ምርኮኞች ሆነው በይፋ እንዲታዩ አደረጋቸው፤»

ምዕ. 5÷6-12 የእግዚአብሔር ታቦት በፍልስጥኤማውያን መካከል በነበረች ጊዜ ፍልስጥኤማውያንን እግዚአብሔር እንደቀሰፈና በእባጭ እንደመታቸው እናነባለን፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው የእግዚአብሔር ሕዝብ ቢሸነፍና ቢማረክም እግዚአብሔርና ቃሉ እንደማይማረኩ ነው፡፡ ጳውሎስ በእስር ቤት በሰንሰለት ታስሮ «የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሠርም» 2ጢሞ. 2÷9 አለ፡፡

## <u>በምዕራፍ ስድስት</u>

የእግዚአብሔር እጅ በፍልስጥኤማውያን ላይ ስለ ከበደች ፍልስኤማውያን የበደል መስዋዕት አድርገው የእግዚአብሔርን ታቦት በሰረገላ ወደ እስራኤል እንደመለሱት እናነባለን፡፡

ቁ. 3- «የእስራኤልን አምላክ ታቦት ብትሰድዱ የበደል መስዋዕት መልሱለት እንጂ ባዶውን አትስደዱት፣ የዚያን ጊዜ ትፈወሳላችሁ» ፍልስጥኤማውያን፣ በእግዚአብሔር ታቦት ላይ ምን እናድርግ? ብለው ካህናትንና ምዋርተኞችን ሲጠይቁ ያገኙት መልስ ነበረ፡፡ ከዚህ ቁጥር የምናየው ነገር ቢኖር ፍልስጥኤማውያን ምንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ባይሆኑም ስለ ሙሴ ሕግና መስዋዕት ባያውቁም እግዚአብሔርን ስለፈሩ ስለ በደላቸው የበደልን መሥዋዕት (በዘሌዋውያን ላይ ካሉት አምስት መስዋዕቶች አንደኛውን) ሲያቀርቡ እስራኤላውያን ግን ሕጉም ቃል ኪዳኑም ለእነርሱ ተሰጥቶ በበደላቸው ምክንያት ተማረኩ እንጂ የበደልን መስዋዕት ስለ በደላቸው አላቀረቡም፡፡ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ባዶ ትምክህት ነበራቸው እንጂ ቃል ኪዳኑ የሚያዛቸውን ትእዛዝ አልፈጸሙም፡፡

ቀ.5፦ በተጨማሪም የፍልስጥኤማውያን ካህናት ፍልስጥኤማውያንን «ለእስራኤል አምላክ ክብርን ስጡ» ብለው ይመክሩአቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ይልቅ አሕዛብ ለእግዚአብሔር ክብርን ይሰጣሉ፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ሲያሳዝን የእግዚአብሔር ሕዝብ ያልሆኑት ግን ለእግዚአብሔር ክብር ሲሰጡ ነው የምናየው፡፡ በዮናስ ሕይወትም ይህንን እናያለን፡፡ ዮናስ 1÷5-6፤ 10፤16 በዚህ ክፍል አሕዛብ ከዮናስ ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት ያሳያሉ፡፡

ምዕ. 6÷10-12 በዚህ ክፍል፤ ፍልስጥኤማውያን ሁለት የሚያጠቡ ላሞችን ወስደው ታቦቱን በሰረገላ ላይ በማድረግ ላሞቹ ሰረገላውን እየጎተቱ እንደዲሄዱ ሲያደርጉ እናያለን፡፡ የሚጠቡትን እንስሶቻቸውን ከእናታቸው ለይተው በቤት ከዘጉባቸው በኋላ ነበር ይህን ያደረጉት፡፡

ቁ. 12 «ላሞቹም ወደ ቤተ ሳሚስ ወደሚወስደው መንገድ አቅንተው እምቧ እያሉ በጎዳናው ላይ ሄዱ ወደ ቀኝም ወደ ግራ አላሉም።» የተፈጥሮ ስሜታቸውን ብንመለከት ከሚጠቡ እንስሶቻቸው በግድ የተለዩ ስለሆኑ ወደ እንስሶቻቸው ለመመለስ ፍላጎት ስለሚኖራቸው ጥረት ማድረጋቸው አይቀርም፤ ነገር ግን የተለዩት ለከበረ ሥራ ስለነበረ በእግዚአብሔር ታቦት ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ክብርና መንፈስ በእነርሱም ላይ ስለነበር ያላቸውን የተፈጥሮ ስሜትና ፍላጎት (የእናትነት ስሜት) አሸንፎ የእግዚአብሔርን ታቦት በደስታ ተሸክመው እንዲሄዱ አደረጋቸው። «እምቧ እያሉ በጎዳናው ላይ ሄዱ፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላሉም።»

እኛም የእግዚአብሔርን ቀንበር በምንሸከምበት ጊዜ ምድራዊና ተፈጥሮአዊ የሆነውን ስሜታችንን አሸንፎ ወደ ታለመልን አቅጣጫ እያዜምንና እግዚአብሔርን እያመሰገንን ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሳንል እንድንሄድ ያደርገናል።

«ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና፤ ለነፍሳችሁ ዕረፍትን ታገኛላችሁ።» ማቴ. 11÷29-30 የጌታ ቀንበር፤ «እምቧ» እያስባለ የሚያስኬደን ነው።

በቁ. 19-20 የሚያሳዝን ቃል እናነባለን፤
«ወደ እግዚአብሔርም ታቦት ውስጥ ተመልክተዋልና የቤትሳሚስን ሰዎች መታ ... የቤትሳሚስም ሰዎች በዚህ በቅዱስ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማን ይችላል? አሉ።» ታቦቱ የሚቀመጥበት ቦታ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እንደነበረና በዚያም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሊቀ ካህኑ መሥዋዕት ለማቅረብ እንደሚገባ በዘሌ 16 እናነባለን። ወደ ታቦቱ ውስጥ ለመመልከት ለማንም አልተፈቀደም። እነዚህ የቤትሳሚስ ሰዎች ግን የድፍረት ኀጢአትን ሲሠሩ እናያለን። ወዳልተፈቀደላቸው ቦታ ተመልከቱ፤ የኀጢአታቸውንም ዋጋ ተቀበሉ።

በአዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ ቅድስት እንድንገባ እንደተፈቀደልን እናያለን።ዕብ. 10÷19-22 በክርስቶስ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከታች ተቀዷልና።

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

በዚህ ምዕራፍ የምናየው፤ በሳሙኤል አሳሳቢነት እስራኤል ሁሉ ከጣዖቶቻቸው ተለይተውና ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱና በጠላቶቻቸው ላይ እግዚአብሔር ድልን ሲሰጣቸውና፣ ምርኮአቸውንም ሲመልስ ነው።

ከቁ. 1-2 እግዚአብሔርን አዝኖ መከተል።

ጣዖት በሕይወታችን ካለና በግማሽ ልብ እግዚአብሔርን የምናመልክ ከሆነ እግዚአብሔርን የምንከተለው በኀዘን ይሆናል።

ከቁ. 3-6 ተሐድሶና ንስሐ

በሳሙኤል አሳሳቢነት እስራኤል ሁሉ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስና፣ ጣዖትን ሲያርቅ እናያለን።

ከቁ. 7-10ሀ፡ - የጠላት ውጊያ
የእግዚአብሔር ሕዝብ በንስሐና በሙሉ ልብ ወደ እግዚአብሔር በሚመለስበት ጊዜ ጠላት ሁልጊዜ ውጊያን ያስነሳብናል። ወደ እግዚአብሔር በቀረብን መጠን ጠላት ሊዋጋን ይሞክራል።

ከቁ. 10ለ-11፡ - እግዚአብሔር ራሱ ለሕዝቡ ይዋጋል።
እኛ ወደ እግዚአብሔር ከቀረብን፣ ጠላት እኛን ለመዋጋት ሲቀርብ የሚያገኘው እግዚአብሔርን ነው። ብዙ ጊዜ ጠላት እኛን ብቻ አግኝቶ የሚዋጋን ከእግዚአብሔር ጋር ቅርበት ስለሌለን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ከቀረብን ጠላት ብቻችንን አያገኘንም።
«እግዚአብሔርም በዚያች ቀን በፍልስጥኤማውያን ላይ ታላቅ ነጐድጓድ አንጐዳጐደ አስደነገጣቸውም በእስራኤልም ፊት ተመቱ።»

ከቁ 12-14 እስራኤል ምርኮና ድልን ያገኛሉ «... ፍልስጥኤማውያንም ተዋረዱ ... ከእስራኤል የወሰዱአቸው ከተሞች ለእስራኤል ተመለሱ፤ እስራኤልም ድንበሩን ከፍልስጥኤማውያን እጅ አዳነ»

በአጠቃላይ ከዚህ ምዕራፍ የምናየው፤

1. ጣዖቶቻችንን በልባችን ይዘን በደስታ እግዚአብሔርን መከተል እንደማንችል «የእስራኤልም ቤት ሁሉ አዝኖ እግዚአብሔርን ተከተለ» (ቁ. 2)
2. ንስሐ ስንገባና ጣዖቶቻችንን ከእኛ ስናርቅ ጠላት አዲስ ውጊያን እንደሚያመጣብን
3. ወደ እግዚአብሔር ስለቀረብን፤ እግዚአብሔር ራሱ ለእኛ እንደሚዋጋልን
4. እግዚአብሔር በጠላታችን ላይ ድልን እንደሚያጐናጽፈንና ምርኮአችንን ሁሉ እንደሚመልስ።

በመግቢያው ላይ እንደጠቀስነው ከምዕ 8-15 ድረስ የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ሳዖል ላይ የሚያተኩር ክፍል ነው።

# ክፍል ሁለት

<u>የንጉሥ ሳዖል መንገሥና መውደቅ ምዕ. 8-15</u>

## <u>ምዕራፍ ስምንት</u>

እስራኤላውያን ወደ ሳሙኤል መጥተው ንጉሥ አንግሥልን እንዳሉት ይናገራል። በዚህ ምዕራፍ የምናየው፤ ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን በእስራኤል ላይ ፈራጆች እንዳደረጋቸው፤ ነገር ግን እነርሱ እንደ አባታቸው በቅንነት የሚፈርዱ እንዳልነበሩ ነው።

ቁ. 3 «<u>ልጆቹም በመንገዱ አልሄዱም</u>። ነገር ግን ረብ ለማግኘት ፈቀቅ አሉ፣ ጉቦም እየተቀበሉ ፍርድን ያጣምሙ ነበር።» ምናልባት ለልጆቹ ጠማማነት ሳሙኤል ተጠያቂ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ጠማማነታቸውን እያወቀ በሥልጣን ላይ ሊያስቀምጣቸው አይገባም ነበረ። ጠ ማማነታቸውን ካላወቀ ደግሞ የገዛ ራሱን ልጆች ማንነት አለማወቁ ራሱ ጥፋት ነው። አንድ ወላጅ የልጆቹን ማንነት ከውጭ እንዲነገረው አይገባም፤ እራሱ ማንነታቸውን አውቆ የሚያስፈልገውን እርምጃ መውሰድ አለበት።

ሳሙኤል፣ እግዚአብሔር ለዔሊ ስለ ልጆቹ የተናገረውን በደንብ ያውቃል፣ ነገር ግን የራሱ ልጆች ፍርድን ሲያጣምሙና ሕዝቡን ሲበድሉ አላወቀም ወይም ችላ አለ፡፡ በዚህ ምክንያት ሕዝቡ ወደ ሳሙኤል መጥተው «አንተ ሸምግለሃል፣ ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም፤ አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን አሉት፡፡» ይህንን ጥያቄ ስንመለከት፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ የጠየቁት ጥያቄ ሳሙኤልንም ሆነ እግዚአብሔርን ቢያሳዝንም የጠየቁበት ምክንያት ግን ዋጋ ያለው ነጥብ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተሾሙ ሰዎች ፍርድን በሚያጣምሙበት ጊዜ፣ ፍትህ ከእግዚአብሔር ሰዎች በሚርቅበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጤናማ ያልሆነ መፍትሔ ለማግኘት ይሞክራል፡፡ መፍትሔው ጤናማ ባይሆንም ይህንን መፍትሔ የጠየቁበት ምክንያት ግን ሊዘነጋ አይገባም፡፡

ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ እግዚአብሔርን ወክሎ በሕዝብ ላይ የሚሾሙ ሰዎች ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብም ሆነ ከእግዚአብሔር ለማራቅ ምክንያት እንደሚሆኑ ነው፡፡

ቁ. 7. «እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፡- በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ፡፡»

## <u>ምዕራፍ ዘጠኝ</u>፡ -

በዚህ ምዕራፍ የምናየው እግዚአብሔር በራሱ ሰማያዊ አሠራር ሳሙኤንና ሳዖልን ሲያገናኝ ነው፡፡

-የሳዖል አባት የቂስ አህዮች ስለጠፉ ሳዖልንና አንድ ብላቴና አህዮቹን ፍለጋ ሲዞሩ ሳሙኤል ወዳለበት ከተማ ይደርሳሉ፡፡ ተስፋ ቆርጠው ከመመለሳቸው በፊት ብላቴናው «አንድ የእግዚአብሔር ሰው በዚህች ከተማ አለ .. ምናልባት የምንሄድበትን መንገድ ይነግረናል» የሚል ሐሳብ ይሰነዝራል፡፡ ይህም ሐሳብ ከራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሐሳብ እንደነበረ ማስተዋል እንችላለን፡፡

ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ አንዳንድ ጊዜ እኛ በምድራዊ ነገር መጥፋትና መጉደል ስንጨነቅ እግዚአብሔር ግን በዚያ ምድራዊ ነገር መጥፋትና መጉደል ወደ ሰማያዊ ዓላማውና በረከቱ እያቀረበን ሊሆን ይችላል፡፡

በቁ. 16 ላይ እግዚአብሔር በሳሙኤል፤ «ነገ በዚች ሰዓት ከብንያም አገር አንድ ሰው እሰድልሃለሁ» ብሎት ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው፣ የአህዮቹ መጥፋትና የሳዖል አህዮቹን ፍለጋ ሳሙኤል ወዳለበት ከተማ ማምጣት ሁሉ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ቀጠሮ እንደነበረ ነው፡፡

ቁ. 24 «እስከ ተወሰነው ጊዜ ድረስ ለአንተ ተጠብቆአልና እነሆ የተቀመጠልህን በፊትህ አኑረህ ብላ» በዚህ ቃል የምናየው፣ በእግዚአብሔር ለሳዖል አስቀምጦለት የነበረውን ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ በረከት ነው፡፡ ለእያንዳንዳችን፤ እግዚአብሔር ያስቀመጠልን ገና ያልበላነው ዕድል ፈንታ አለ፡፡ በእግዚአብሔር ሐሳብና መንገድ ካልሄድን ግን የተቀመጠልን ዕድል ፈንታ ሊቀርብን ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ አሥር</u>

የሳዖልን መቀባትና በብዙ ምልክቶች እግዚአብሔር ሲያረጋግጥለት እናነባለን፡፡ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ለደኅንነትም ሆነ ለአገልግሎት ሲጠራን፣ ገና ጀማሪዎች ነንና ብዙ ምልክቶችንና ማበረታቻ ነገሮችን ያደርግልናል፤ ካደግን በኋላ ግን በምልክት ሳይሆን ቃሉን

በመታዘዝ እንድንኖር ነው የሚፈለገው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፤ እግዚአብሔር በሳሙኤል በኩል የመጀመሪያውን ትእዛዝ ሲሰጠው እናነባለን።

ቁ. 8 «እኔም የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቀርብ ዘንድ የደኅንነትም መሥዋዕት እሠዋ ዘንድ ወደ አንተ እወርዳለሁ፤ እኔ ወደ አንተ እስክመጣና የምታደርገውን እስክነግርህ ድረስ ሰባት ቀን ትቆያለህ።»

ሳዖል በምዕ. 13 ላይ ሲተላለፍ የምናየው ትእዛዝ ይህንን ነው።

በዚህ ምዕራፍ ቁ. 1 ላይ «ሳሙኤልም የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በራሱ ላይ አፈሰሰው።» ይላል በዚህ ቦታ ከሳሙኤልና ከሳዖል በስተቀር ማንም የለም። ይህ ቅባት በግልና በጓዳ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ቅባት ምሳሌ ነው። ከቁ. 16-27 ደግሞ እግዚአብሔር በአደባባይ ሳዖልን ለንጉሥነት እንደመረጠው ሲመሰክርለት እናያለን። ይህ፤ እግዚአብሔር በወዳጆችም ሆነ በጠላቶቻችን ፊት ለፊት በራሳችን ላይ የሚያፈሰው ቅባት ምሳሌ ነው።

ዳዊት በመዝሙር 23 ላይ «በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ» እንዳለው ዓይነት ቅባት ነው።

በዚያ ሥፍራ ወዳጆችም ጠላቶችም እንደነበሩ በቁ 26ና 27 እንረዳለን።

«... እግዚአብሔር ልባቸውን የነካ ኃያላንም ከእርሱ ጋር ሄዱ። ምናምንቴዎች ሰዎች ግን፡ - ይህ ሰው እንዴት ያድነናል? ብለው ናቁት፣ እጅ መንሻም አላመጡለትም።»

በምዕ. 11÷14-15 ላይ ደግሞ ሕዝቡ ሳዖልን በእግዚአብሔር ፊት ሲያነግሡት እናያለን።

- ❖ (ምዕ. 10÷1) በመጀመሪያ እግዚአብሔር በጓዳ ቀባው
- ❖ (ምዕ. 10÷24) በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር በአደባባይ በሕዝቡ ፊት ሞገስን ሰጠው (ቀባው)
- ❖ (ምዕ. 11÷14-15) ሕዝቡ አነገሡት (ቀቡት)

በዳዊትም ሕይወት ተመሳሳይ የሆነ የመቀባት ደረጃዎችን እናያለን።

- (ምዕ. 16÷13) በመጀመሪያ በሳሙኤል ተቀባ
- (2ሳሙ 2÷4) ቀጥሎ የይሁዳ ሰዎች ቀቡት
- (2ሳሙ 5÷3) በመጨረሻም በእስራኤል ሁሉ እንዲነግሥ ቀቡት።

## ምዕራፍ አስራ አንድ

የሳዖል የመጀመሪያው ቀን ውጊያና ድል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ወርዶ ለጦርነት ሲነሳና ሕዝቡንም ሲያነሳሳ እናያለን። እግዚአብሔርንም በሕዝቡ ፊት ከፍ ከፍ አደረገው ወደ ጌልጌላም ተሰብስበው አነገሡት። «በዚያም ሳዖልና የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ታላቅ ደስታ አደረጉ።» (ቁ. 15)

በዚህ ምዕራፍ በኢያቢስ ገለዓድ የነበሩ እስራኤላውያን በአሞናዊ ናዖስ ሊወረሩ ሲሉ ወደ እስራኤል ሁሉ መልእክተኛ ልከው እርዳታ ከጠየቁ በኋላ እግዚአብሔር በሳዖል በኩል ድልን ሲሰጣቸው እናያለን።

መልእክተኞቹ መጥተው ለሕዝቡ ከተናገሩ በኋላ፤

ቁ. 4 «... ሕዝቡም ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ።» ጥቃቱ በቀጥታ ወደ እነርሱ ባይመጣም በወገኖቻቸው ላይ ሊመጣ ስላለው ጥቃት ሲያለቅሱ እናያለን። የእግዚአብሔር ቃል፤ አንዱ ብልት ሲሰቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ፤ 1ቆሮ 12÷6 የሚለውን

በተግባር ያሳየናል። አባቶችም ሲተርቱ «አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል» እንዳሉት ነው። ቡጢው የተሰነዘረባቸው የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ናቸው፣ የሚያለቅሱት ግን የጊብዓ (ሳዖል የነበረበት ከተማ) ሰዎች ናቸው።

በተጨማሪም የእግዚአብሔር ቃል በመከራ ያሉትን እናንተ ራሳችሁ በመከራ እንዳላችሁ አድርጋችሁ አስቡአቸው ይለናል።
ሳዖልም ከእርሻው ሲመለስ፤ «ሕዝቡ የሚያለቅስ ምን ሆኖ ነው? አለ» (ቁ. 5) መሪ የሆነ ሰው ሁልጊዜ የሚመራውን ሕዝብ ስሜት መረዳት መንከባከብ አለበት። ሕዝቡም የኢያቢስን ሰዎች ጥቃት በነገሩት ጊዜ ቁ. 6 «ይህንም ነገር በሰማው ጊዜ በሳዖል ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደ ቁጣውም እጅግ ነደደ።»

የእግዚአብሔር መንፈስ ሁልጊዜ የተጠራንበትን ዓላማ ከግብ እንድናደርስ ከእኛ ጋር ይተባበራል፣ የሚያስፈልገንን ኃይልና ጸጋም በሚያስፈልገን ጊዜ ይሰጠናል። «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» የሚለን ስለዚህ ነው።

በእግዚአብሔር መንፈስ እርዳታ ድልን ሲጎናጸፉ እናነባለን።

<u>ምዕራፍ አስራ ሁለት</u>፡ -

ሳሙኤል እስራኤልን ሁሉ ሰብስቦ ያስጠነቅቃቸዋል። ንጉሥ እንዲነግሥላቸው በመለመናቸው ታላቅ ክፋት እንዳደረጉ ከነገራቸው በኋላ የበደላቸውን ታላቅነት እንዲገነዘቡ፤

ቁ. 18 «ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ እግዚአብሔርም በዚያን ቀን ነጎድጓዱ ዝናብ ላከ፤ ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርንና ሳሙኤልን እጅግ ፈሩአቸው።» ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቁ የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ክብርና ቅድስና ለሕዝቡ ስለሚገልጽ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን እነርሱንም የሚያከብርና የሚፈራ ይሆናል። እግዚአብሔርም ሞገሱንና መፈራቱን በእነርሱ ላይ ያደርጋል።

ሕዝቡ ከመፍራታቸው የተነሣ፤ «ንጉሥ በመለመናችን በኃጢአታችን ሁሉ ላይ ይህን ክፋት ጨምረናልና እንዳንሞት ስለ ባሪያዎችህ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ አሉት» ቁ. 19። ሳሙኤል ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ስም ሲጠራ «አምላካችሁ እግዚአብሔር» (ቁ. 2) ይላቸዋል፤ ይህም እግዚአብሔር አምላካቸው እንደሆነ ደግሞ ደጋግሞ ሊያሳስባቸው ነው። እነርሱ ግን «ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ» ይሉታል። ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር አምላክነት ሥር እንዳልሆኑ ያሳያል።

ሳሙኤልም፤ «እግዚአብሔር ለእርሱ ሕዝብ ያደርጋችሁ ዘንድ ወዷልና እግዚአብሔር ስለ ታላቅ ስሙ ሕዝቡን አይተውም።» (ቁ. 22) ይላቸዋል። እግዚአብሔር የማይተዋችሁ ስለ ጽድቃችሁ ሳይሆን ስለ ወደዳችሁና ስለ ታላቅ ስሙ ሲል ነው ይላቸዋል።
በአዲስ ኪዳንም ስንመጣ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለዓለም ሁሉ የሰጠው «እንዲያው ስለወደደን» ብቻ እንደሆነ ይነግረናል (ዮሐ. 3፥16)

በተጨማሪም፤ ሳሙኤል እረኛ እንዲሆናቸው ለተሰጠው ሕዝብ አለመጸለይ እግዚአብሔርን መበደል ወይም ኀጢአት እንደሆነ ሲገልጽ፤ «ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ።» ይላቸዋል (ቁ. 23)።

ከዚህ ምዕራፍ ሌላ የምናስተውለው ነገር፤ በቁ. 11 ላይ ሳሙኤል፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን ስለላካቸው ሰዎች ሲናገር፤ ይሩበአልን (ማለትም ጌድዮንን) ባርቅን፣

የፍታሔንና ራሱን ብቻ ይጠቅሳል። በመጽሐፈ መሳፍንት እንደተመለከትነው 12ት የሚሆኑ መሳፍንቶች ሲኖሩ ከነዚያ ውስጥ በተለይ 6ቱ ጎልተው እንደሚታዩ ተመልክተን ነበር። በዚህ ክፍል ከ6ቱም ሦስቱን ብቻ ሲጠቅስ እናያለን። በተለይ ሳምሶንን ከዚህ ዝርዝር አለማየታችን፣ እዚህ ላይ ሳሙኤል የዘረዘረው እግዚአብሔርን ያለማመንታትና ያለማሳዘን ያገለገሉትንና ደስ ያሰኙትን መሳፍንት ብቻ መጥቀሱ ሳይሆን አይቀርም።

ማንም ሰው ቢሆን እግዚአብሔርን ማገልገል ይችላል፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙና በልቡ ያለውን ሁሉ የሚያደርጉ በጣም ጥቂት ናቸው። ኢየሱስ በመልካም መሬት ስለተዘራው ዘር ሲናገር፤ «አንዱ 30 አንዱ 60 አንዱ ደግሞ 100 ፍሬ አፈራ» አለ። የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ 100 ፍሬ እንድናፈራ ነው።

ሳሙኤል ከሦስቱ መሳፍንት ጋር እራሱንም መጨመሩ፤ የራሱን ማንነት በእግዚአብሔር ፊት ስለሚያውቅና ከአጉል ትህትና ነጻ ስለነበረ ነው። የሆነውን ያህል ነኝ ማለት ትዕቢት አይደለም።

## ምዕራፍ አስራ ሦስት

የሳዖል የመጀመሪያው ውድቀት፤ ሳዖል መታገሥ አቅቶት ያለ ቅባቱና ያለ ጥሪው መሥዋዕት ያቀርባል። በምዕ. 10÷8 ላይ ሳሙኤል፤

1. የሚቃጠለውን መሥዋዕት የሚያቀርበው እራሱ እንደሆነ፤
2. እስኪመጣ ድረስ 7ቀን እንዲጠብቀው አስጠንቅቆት ነበር።

የሳዖል ቅባት የንጉሥነት ቅባት፤ ማለትም ሕዝቡን የማስተዳደር፤ እንጂ የክህነት ቅባት አልነበረም። ባልተፈቀደለትና በማያገባው አገልግሎት ውስጥ ገብቶ እናያለን። ይህም መተላለፉ ለዘላለም ሊሰጠው የነበረውን በረከት እንዳስቀረበት ሳሙኤል ይነግረዋል፤ ቁ. 13፤14 «ሳሙኤልም፣ ሳዖልን አላበጀህም አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህም፤ <u>ዛሬ</u> እግዚአብሔር መንግሥትህን በእስራኤል ላይ <u>ለዘላለም አጽንቶልህ ነበር</u> አሁንም መንግሥትህ አይጸናም።»
በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ካሉት አሳዛኝ ጥቅሶች አንዱ ይህ ነው። አንድ ጊዜ በአለመታገስና በአመጽ የምናደርገው ድርጊት የዘላለም በረከትን ሊያስቀርብን ይችላል።

በሳዖል ሕይወት ይህ አሳዛኝ ውድቀት የደረሰበት በነገሠ በሁለት ዓመቱ ነው። ሳዖል በአጠቃላይ የነገሠው ለ40 ዓመታት ቢሆንም፣ 38ቱን ዓመታት የነገሠው የእግዚአብሔር ሞገስ ከእርሱ ተለይቶ እንደነበረ እናያለን። በእስራኤላውያን ላይም ተመሳሳይ ውድቀት ደርሶባቸው እንደነበረ ከዘኍልቁ መጽሐፍ ተመልክተናል። ከግብጽ በወጡ በሁለተኛው ዓመታቸው እግዚአብሔር በቃዴስ በርኔ የፈተናቸውን ፈተና ስለወደቁ ወይም ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት እግዚአብሔርን ስላልተማመኑ ለቀሩት 38 ዓመታት በምድረ በዳ ሲቅበዘበዙ እናያለን። (ዘኍ. 13 እና 14) እኛም በእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ ላይ ካመጽን ያለ ሞገስ ሕይወታችንን ልንፈጅ እንችላለን። እግዚአብሔርን 40 ዓመት ልናገለግለው እንችላለን ነገር ግን አገልግሎታችን ዓመጽና አለመታዘዝ ካለበት የምድረበዳ አገልግሎት ይሆንብናል።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ፤ እንደ ሳዖል ሹመቱንና ቅባቱን ሳይጠብቅ በማይገባው ገብቶ የተቀሰፈ ሌላ ንጉሥ እንዳለ እናያለን። (1ዜና 26÷16-21)

«ነገር ግን በበረታ ጊዜ ለጥፋት ልቡ ታበየ አምላኩንም እግዚአብሔርን በደለ ወደ መቅደስ ገብቶ በዕጣን መሠዊያ ላይ ዐጠነ። ካህኑም ዓዛርያስ ከእርሱም ጋር ጽኑዓን የነበሩ

ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት ተከትለው ገቡ። ንጉሡንም ዖዝያንን እየተቃወሙ፤ ዖዝያን ሆይ ዕጣን ማጠን የተቀደሱት የአሮን ልጆች የካህናት ሹመት ነው እንጂ ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ አይገባህም፤ በድለሃልና ከመቅደሱ ውጣ ከአምላክህም ከእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አይሆንልህም አሉት። ዖዝያንም ተቆጣ ... ካህናትንም በተቆጣ ጊዜ በካህናቱ ፊት ... በግምባሩ ላይ ለምጽ ታየ። ... እግዚአብሔርም ቀስፎት ነበርና ይወጣ ዘንድ ቸኮለ። እስኪሞት ድረስ ለምጻም ነበር።»

ከ1ኛ ሳሙኤል 13 ሌላ የምንማረው ትምህርት፤ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ መታመናችን በእርሱ ላይ ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ የምንታመንባቸውንና የምንደገፍባቸውን ነገሮች ሁሉ ከእኛ የሚያርቅበት ጊዜ እንዳለ ነው። ሳዖል፤ ልቡ በሳሙኤልና በሕዝቡ ላይ እንጂ በእግዚአብሔር ላይ ስላልተደገፈ ሕዝቡ በሸሸና ሳሙኤል በዘገየ ጊዜ መታገስና ጸንቶ እግዚአብሔርን መጠበቅ ተሳነው። እኛስ፤ የምንተማመንባቸው ነገሮች ሁሉ ከእኛ ሲሸሹ፤ ተስፋ የምናደርገው ነገር ሲዘገይ ፊተናውን እናልፍ ይሆን? በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ተደግፈን፤ «ቢገድለኝም እንኳን እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ።» (ኢዮብ 13፥15) ለማለት ያብቃን።

## <u>ምዕራፍ አስራ አራት</u>

ዮናታን ከጋሻ ጃግሬው ጋር ሆኖ የእምነት እርምጃ በመውሰድ ፍልስጥኤማውያንን እንዳሸነፈ።

ቁ. 1 «... ለአባቱም አልነገረውም።» እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮችን በልባችን ሲያስቀምጥ ለማን መንገር እንዳለብንና ለማን መንገር እንደሌለብን ማወቅ አለብን። የዮናታን አባት፣ ሳዖል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሶ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሞገስ ውጭ የነበረ ሰው ስለነበረ፣ ለእርሱ መንገር የእግዚአብሔርን ሐሳብ ማጨናገፍ ይሆን ነበር።

ለጋሻ ጃግሬው የነገረበትን ምክንያት በቁጥር 7 ላይ እናያለን። «ጋሻ ጃግሬውም ልብህ ያሰኘህን ሁሉ አድርግ እነሆ ከአንተ ጋር ነኝ፤ <u>እንደ አንተ ልብ ሁሉ የእኔም ልብ እንዲሁ ነው</u> አለው።»
የጋሻ ጃግሬው ልብ ከእርሱ ጋር እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው እግዚአብሔር በልቡ ያስቀመጠውን የነገረው። ፍጹም አንድ ልብ የሆኑ ሁለት ሰዎችን እግዚአብሔር ሲያገኝ በእነዚያ ሰዎች ድንቅ ነገር ማድረግ ይችላል። ስለዚህ ነው በአዲስ ኪዳን፣ ጌታ፤ «ከእናንተ <u>ሁለቱ</u> በምድር <u>በማናቸውም</u> በ<u>ሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ</u> በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል» ያለው። (ማቴ. 18፥19)።

ዮናታን፤ በጣም ብዙ የነበሩትን ፍልስጥኤማውያን ሲያይ፤ ብዛታቸውንና የጦር መሣሪያቸውን ብዛት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሌላቸው አሕዛቦች መሆናቸውን ነበር ያስተዋለው።

ቁ. 6 «ዮናታንም ጋሻ ጃግሬውን፡ - ና <u>ወደ እነዚህ ቆላፋን ጭፍራ እንለፍ</u> በብዙ ወይም በጥቂት ማዳን እግዚአብሔርን አያስቸግረውምና።» ከእግዚአብሔር ጋር የቃል ኪዳን ምልክት የነበረውን የግዝረት ሥርዓት የማያውቁ እንደሆኑ ማመልከቱ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፤ ኢያሱና ካሌብ ከአሥሩ ሰላዮች ጋር ሆነው የተስፋይቱን ምድር ከሰለሉ በኋላ፣ አስሩ በምድሪቱ የነበሩትን ሰዎች ትልቅነትና አስፈሪነት ሲናገሩ፤ ኢያሱና ካሌብ ግን፤ «እንደ እንጀራ ይሆኑልናልና የምድሪቱን ሰዎች አትፍሩ፤ ጥላቸው ከላያቸው ተገፏል» ብለው ነበር የተናገሩት። ዮናታንም በሥጋ ዓይን የሚታየውን ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዓይን የማይታየውን ነበር የተመለከተው።

በአዲስ ኪዳን ላለነው የእግዚአብሔር ቃል፤ «በእናንተ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል» ይለናል (1ኛ ዮሐ. 4፥4)።

የናታንና ጋሻ ጃግሬው በወሰዱት የእምነት እርምጃ

1. እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ላይ ታላቅ ድልን ሰጣቸው።

2. ፈርተውና በየዋሻው ተሸሽገው የነበሩት እስራኤላውያን ሁሉ ከተሸሸጉበት ወጥተው መዋጋት ጀመሩ።

ቁ 22 «... የተሸሸጉት ሁሉ ... ሊዋጉአቸው ተከትለውት ገሠገሡ። እኛ በእግዚአብሔር ላይ ታምነን በምንወጣበት ጊዜ ብዙዎቹን እንደምናነቃቃ፣ እግዚአብሔርም ከተሸሸጉበት የፍርሃት ዋሻ እንደሚያወጣቸው እናያለን።

ከቁ. 24 ጀምሮ የምናየው ሐሳብ፤ ሳዖል ከእግዚአብሔር ባልሆነ መሐላ ሕዝቡን ሲያስርና ሲያስጨንቅ ዮናታንም በአባቱ ሲያማርር ነው። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆነ ሰው መልካም ነው ብሎ የሚያደርገው ነገር እንኳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያስቸግር ይሆናል።

ሳዖል «ጠላቶቼን እስክበቀል እስከማታ ድረስ የሚበላ ሰው ርጉም ይሁን ብሎ ሕዝቡን አምሎአቸው ነበር።» ቁ. 24 «ዮናታንም፡ - አባቴ ምድሪቱን አስቸገረ፤ ከዚህ ማር ብቀምስ ዓይኔ እንደበራ እዩ። ይልቅስ ሕዝቡ ካገኙት ከጠላቶቻቸው ምርኮ በልተው ቢሆኑ የፍልስጥኤማውያን መመታት ይበልጥ አልነበረምን አለ» (ቁ. 29-30)። ከዚህ ሁኔታ የምናየው፤ ከሥጋና ከደም የሆነ ሥርዐትና ወግ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚያስርና እንደሚያስጨንቅ ነው።

በአንፃሩ ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ሥርዓት ቀን እንደሆነና ልብንም ደስ እንደሚያሰኝ በመዝ. 18(19)፡8 ላይ እናነባለን።
ምዕ. 15፡ - የሳዖል ሁለተኛው ውድቀት፡ -
እግዚአብሔር ከብዙ ዘመናት በፊት (ከ400 ዓመታት በላይ) ስለ አማሌቅ መደምሰስ የተናገረውን እንዲፈጽም በሳሙኤል በኩል ለሳዖል ይነግረዋል።

ቁ. 2 «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ - እስራኤል ከግብጽ በወጣ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ እየተቃወመ ያደረገበትን እበቀላለሁ። አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ አትማራቸውም ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕፃኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል።»

ከዚህ ክፍል የምናየው እግዚአብሔር በእውነትም የበቀል አምላክ እንደሆነ ነው። «በቀል የእኔ ነው» ያለ አምላክ፣ ከ400 ዓመታት በፊት አማሌቅ በእስራኤላውያን ላይ ያደረገውን እበቀላለሁ እንዳለ ያንን ትእዛዝ የሚፈጽምለትን ሰው ሲፈልግና ሲያዝ እናያለን።
<u>ዘጸ. 17÷14</u> «እግዚአብሔር ሙሴን፡ - የአማሌቅን ዝክር ከሰማይ በታች ጨርሼ እደመስሳለሁና ይህ ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፈው በኢያሱም ጆሮ ተናገረው»

<u>ዘዳ 25÷17-19</u> «ከግብጽ በወጣችሁ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ ላይ ያደረገብህን አስብ፤ በመንገድ ላይ እንደተቃወመህ አንተም ተስኖህ ደክመህም ሳለህ ከአንተ በኋላ ደክመው የነበሩትን ሁሉ እንደመታ እግዚአብሔርንም አልፈራም። ስለዚህ አምላክህ እግዚአብሔር ትወርሳት ዘንድ በሚሰጥህ ምድር ከሚከብቡህ ጠላቶችህ ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ባሳረፈህ ጊዜ የአማሌቅን ዝክረ ስሙን ከሰማይ በታች አጥፋው፤ ይህንን አትርሳ።» እግዚአብሔር በሳዖል «አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣ አትማራቸውም ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕፃኑን ግደል።» ሲል፤ ብላቴውና ሕፃኑ ምን አድርጎ ወይ ምን አውቆ ነው?

ማለት ይቻላል:: ነገር ግን አማሌቅ በእስራኤል ላይ ያደረገውን ዓይነት ጥፋት በራሱ ላይ ሲደርስበት ነው የምናየው::

አማሌቅ፤ ደክመው የነበሩትን፣ ከኋላ ሲጓዝ የነበሩትን መታ ሲል: - ሽማግሌዎችን፣ ሴቶችን ብላቴኖችንና ሕፃናትን ያመለክታል:: እግዚአብሔር ያስተላለፈው ቅጣት ከተደረገው ወንጀል ጋር ተመጣጣኝ እንደሆነ ነው የምናየው::

ያዕ. 2÷13 «ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምህረትም በፍርድ ላይ ይመካል::» የአማሌቅ ፍርድ ምህረት የሌለበት ስለነበር የደረሰበትም ፍርድ ምሕረት የሌለበት ነው::

ስለ አማሌቅ፤ «እግዚአብሔርንም አልፈራም» ይላል: - ምሕረት አልነበረውም ማለት ነው ለሳዖል ደግሞ «ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፤ አትማራቸውም» አለው::

ሳዖል ግን ለንጉሡ ለአጋግና ለመልካሞቹ በጎችና በሬዎች በመራራት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመፈጸም ተመለሰ::

ቁ. 10-11 «የእግዚአብሔርም ቃል ሳዖል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥኩት ተጸጸትኩ ብሎ ወደ ሳሙኤል መጣ» ቁንጽል የሆነ መታዘዝ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አለመታዘዝ ይቆጠራል:: የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሙሉ ለሙሉ እንፈጽማለን፤ ወይም በትእዛዙ ላይ እናምጻለን:: <u>ግማሽ መታዘዝ የሚባል ነገር የለም</u>::

የሳዖል ትልቁ ችግር ስህተቱንና ኃጢአቱን አለማወቁ፣ አለማስተዋሉና አለመቀበሉ ነው::

ቁ. 13-14 «ሳዖልም: - አንተ ለእግዚአብሔር የተባረክህ ሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሜአለሁ አለው:: ሳሙኤልም ይህ በጆሮዬ የምሰማው የበጎች ጩኸትና የበሬዎች ግሣት ምንድር ነው? አለ::» በጓዳችን አመጻችንን ሸሽገን «የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሜአለሁ» ማለት እንችላለን::

ቁ. 19 «ለምርኮ ሳስተህ ለምን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህም?» እኛስ ምን አሳስቶን ወይስ ምን በልጦብን ይሆን የእግዚአብሔርን <u>ትእዛዝ የማንፈጽመው? ዳዊት በአንጻሩ «ትእዛዝህን ለመፈጸም ጨከንኩ አልዘገየሁምም</u>» ይላል::

ሳዖል ግን «አትማራቸው» ለተባለው ነገር፤ «ነገር ግን ሳዖልና ሕዝቡ፤ ለአጋግ ለተመረጡትም በጎችና በሬዎች ለሰቡትም ጥጆችና ጠቦቶች ለመልካሞቹም ሁሉ <u>ራሩላቸው</u>፣ ፈጽሞ ሊያጠፉአቸውም አልወደዱም::» ቁ. 9
ከእግዚአብሔር የበለጠ መሐሪና ሩኅሩኅ የሆንን ሲመስለን ችግር ይመጣል:: እግዚአብሔር ጨክን ሲል መጨከን ያስፈልጋል::

የሳዖል ምክንያት «ሕዝቡ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ይሠዋ ዘንድ መልካሞቹን በጎችና በሬዎች አድነዋቸዋል» የሚል ነበር:: በሕዝቡ ላይ የማላከክ ስሜት አለበት፤ ውሸትም ሳይኖርበት አይቀርም:: ምክንያቱም ቁ. 9 ላይ ስለ ራሩላቸው እንጂ መሥዋዕት ሊያቀርቡ አዳኑአቸው አይልም::

የእግዚአብሔር ባሪያ ሳሙኤል የሰጠው መልስ ግን ለሁላችንም ታላቅ ምክር ያዘለ ቃል ነው::

ቁ. 22-23 «ሳሙኤልም፤ በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመስዋዕት ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል። ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፣ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደማምለክ ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ አለ።»

ሳኦል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፈው «ሕዝቡን ስለ ፈራ» ቁ. 24 እንደነበረ ይናገራል። «ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል» የሚለው ቃል እውነተኛ ቃል ነው።
ሳዖል ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙት የነበረው ሰው ስላልነበረና በግል እግዚአብሔርን ስለማያውቅ ለኀጢአት ይቅርታ የሚጠይቀው ሳሙኤልን እንጂ እግዚአብሔርን አልነበረም፤

ቁ. 25 «አሁንም እባክህ ኀጢአቴን ይቅር በለኝ»
ዳዊት በአንጻሩ፤ በኀጢአት ከወደቀ በኋላ፤
«አቤቱ እንደ ቸርነትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ አንተን ብቻ በደልኩ...» (መዝ. 51) ብሎ ነበር የጸለየው። ልዩነቱ፤ አንዱ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙት ነበረው፤ ሌላኛው ግን እግዚአብሔርን የሚያውቀው በእጅ አዙር ነው።

ሳዖል ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር የሚፈልግ፤ ከእግዚአብሔር ፍርሃት ይልቅ ሕዝቡን የሚፈራ ሰው ነበር፤
ቁ. 30 «እርሱም፡ - በድያለሁ፣ አሁን ግን በሕዝቤ በእሥራኤል ፊት እባክህ አክብረኝ ለአምላክህም ለእግዚአብሔር እሰግድ ዘንድ ከእኔ ጋር ተመለስ አለው።» ሳዖል ማድረግ የነበረበት፤ ለሳሙኤል አምላክ መስገድ ሳይሆን፤ የራሱ የግሉ አምላክ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት በንስሐ መውደቅ ነበር።

ከቁ. 32-34 ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ምን ያህል ቆራጥ እንደነበረ እናያለን።
«ሳሙኤልም፡ - የአማሌቅን ንጉሥ አጋግን አምጣልኝ አለ። አጋግም እየተንቀጠቀጠ ወደ እርሱ መጣ። አጋግም፡ - በውኑ ሞት እንደዚህ መራራ ነውን? አለ። ... ሳሙኤልም አጋግን በእግዚአብሔር ፊት በጌልጌላ ቆራረጠው።»
እግዚአብሔር ዝክረ ስሙ እንዲጠፋ የሚፈልገውን ነገር ሳንራራ ቆራርጠን ማጥፋት አለብን።

## ክፍል III

ዳዊት መቀባቱ፣ ሳዖልን ማገልገሉና፣ መሰደዱ (ከምዕ. 16-31)

ምዕ. 16 የዳዊት መቀባት
ቁ. 1ሀ. «እግዚአብሔርም ሳሙኤልን፡- በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳዖል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው?»
ስንት ጊዜ እንባችንን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በሆነ ነገር አፍስሰናል? እግዚአብሔር ንቆ የጣለውን እኛ የሙጥኝ ብለን እንይዛለን። ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ለመሄድ እግዚአብሔር የናቀውን መናቅ እግዚአብሔር ያከበረውን ማክበር አለብን። መዝ. 14(15)1፤4 ይላል። «አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?
ኃጢአተኛ በፊቱ የተናቀ
እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር»

ቁ. 1ለ. «በቀንድህ ዘይቱን ሞልተህ ሂድ»
ቁ. 3 «የምነግርህንም ቀባልኝ።»
በእግዚአብሔር የተቀቡ ሰዎች ሌሎችን እንዲቀቡ እግዚአብሔር የሚልካቸው ጊዜ አለ። ለሌሎችም የሚተርፍ ቅባት በሕይወታችን መኖር አለበት። እግዚአብሔር በእኛ በኩል ሌሎችን ሊቀባ ይፈልጋል። ዳዊት «ጽዋዬ የተረፈ ነው» አለ። እኛን አረስርሶ ለሌሎች መፍሰስ አለበት።

ቁ. 4 «... የአገሩ ሽማግሌዎችም እየተንቀጠቀጡ ሊገናኙት መጡና፣ የመጣኸው ለደኅንነት ነውን? አሉት።» የእግዚአብሔር ሞገስ በእነርሱ ላይ ያለ የእግዚአብሔር ሰዎች ምን ያህል የተፈሩና የተከበሩ እንደሆኑ እናያለን። እግዚአብሔር ራሱ ሞገሱንና መፈራቱን በእነርሱ ላይ ያደርጋል።

ቁ. 6 «ወደ ኤልያብ ተመልክቶ ፡ - በእውነት እግዚአብሔር የሚቀባው በፊቱ ነው አለ። እግዚአብሔር ግን ሳሙኤልን፤ ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት፤ ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል አለው።» ሳሙኤል፤ ከዚህ በፊት እግዚአብሔር የቀባው ንጉሥ ከሌሎቹ ሁሉ በቁመት ዘለግ ያለ ስለነበር አሁንም ከእሴይ ልጆች ሁሉ ዘለግ ያለውን ይቀባል ብሎ አስቦ ነበር፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር አሠራር በድግግሞሽ ሳይሆን ሁልጊዜ አዲስና የማይመረመር ነው። የእግዚአብሔርን ሐሳብ ላለመረዳትና ላለመፈጸም ዕንቅፋት የሚሆንብን ብዙ ጊዜ ያለፈው ልምምዳችን ነው።

ቁ. 11 «ሳሙኤልም እሴይን፡ - የቀረ ሌላ ልጅ አለህን? አለው። እርሱም፡ - ታናሹ ገና ቀርቷል፤ እነሆም በጎችን ይጠብቃል አለ። ሳሙኤልም እሴይን፤ እርሱ እስኪመጣ አንረፍቅምና ልከህ አስመጣ አለው።» በሰዎች አሳብ ከቁጥር እንኳን የማንገባ ብንሆን በእግዚአብሔር ዓይኖች ከታየን፣ ከተደበቅንበት ቦታ በጊዜውና በሰዓቱ ያወጣናል፣ ይቀባናል ለክብሩም ከፍ ከፍ ያደርገናል።

ቁ. 12-13 «... እግዚአብሔርም ይህ ነውና <u>ተነሥተህ</u> ቀባው አለ። ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው። የእግዚአብሔርም መንፈስ ከዚያ ቀን ጀምሮ በዳዊት ላይ በኃይል መጣ።»

ሳሙኤል በዕድሜ የጠና የሸመገለ ሰው ነበረ፤ ደዊት ደግሞ በዚያን ጊዜ ትንሽ ብላቴና ነበር እግዚአብሔር ለሳሙኤል «ተነሥተህ ቀባው» ይለዋል ብላቴና ለሽማግሌ ይነሣል እንጂ ሽማግሌ ለብላቴና አይነሣም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የመረጠውና ያከበረው ብላቴና ስለነበር «ተነሥተህ ቀባው» ይለዋል።

ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነውና፤ ዳዊት በዘይት በተቀባ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ወረደ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ሳይሆን አይቀርም የአባቱን በጎች ሲጠብቅ አንበሳና ድብ ጠቦት ለመውሰድ ሲመጣ መትቶ ያስጥለውና ይገድለው የነበረው። (ምዕ. 17፥34-35)
ከቁ. 14-23፡ - የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳዖል ስለራቀ ክፉ መንፈስ ሳዖልን ማሠቃየት እንደጀመረ እናያለን። የእግዚአብሔርን መንፈስ የምናሳዝን የምናርቅ ከሆነ ክፉ መንፈስን እየጋበዝን ነው ማለት ነው። መሐል ሰፋሪ መሆን አይቻልም። የእግዚአብሔር መንፈስ ቀርቦን ክፉ መንፈስ ደግሞ ርቆን ወይም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ርቆን ክፉ መንፈስ ደግሞ ቀርቦን እንኖራለን። የእግዚአብሔር መንፈስ የራቀንን ያህል ክፉ መንፈስ ይቀርበናል።
ሳዖል ለነበረበት በክፉ መንፈስ የመሠቃየት ችግር፣ ባሪያዎቹ መልካም መፍትሔን ሲፈልጉ እናነባለን።

መፍትሔውም፤ «መልካም አድርጎ በገና የሚመታ ሰው» መፈለግ ነበር። ማለትም የዝማሬ ቅባት የነበረበት ሰው እንዲዘምርለትና ክፉው መንፈስ ከእርሱ እንዲርቅ ለማድረግ ነው። ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር የተገኘው ሰው ዳዊት ነበር።

<u>ቁ. 23</u> «እንዲህም ሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሳዖል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር፤ ሳዖልንም ደስ ያሰኘው፣ ያሳርፈውም ነበር፣ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።» ከዚህ ጥቅስ በቅባት ስለሚደረግ ዝማሬ የምንረዳው፤

1. መንፈስን ደስ እንደሚያሰኝ
2. ነፍስን እንደሚያሳርፍ
3. ክፉ መንፈስን እንደሚያርቅ

## <u>ምዕራፍ አስራ ሰባት</u>

<u>ዳዊትና ጎልያድ</u>

ጎልያድ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገዳደር የዲያብሎስ ምሳሌ ነው። ጎልያድ ምንም ግዙፍ ቢሆን፣ ምንም ብዙዎችን የሚያስፈራና የሚያንቀጠቅጥ ቢሆንም፤ አምላኩን ለሚያውቅ ለእግዚአብሔር ሰው ግን ከምንም አይቆጠርም።

ብላቴናው ዳዊት ግዙፉን ጎልያድን ሲመለከት እንደሌሎቹ ከመርበድበድ ይልቅ «የሕያውን አምላክ ጭፍሮች የሚገዳደር <u>ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊው ማን ነው</u>?» አለ። ዳዊት ጎልያድን ያየው በመንፈስ እንጂ በሥጋው ግዙፍነት አልነበረም። ጎልያድ ግን ዳዊት ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ «ብላቴና ነበርና ናቀው» ጎልያድ፣ በዳዊት ውስጥ ያለውን ሰማያዊ ኃይል ቢያውቅ ኖሮ ከመናቅ ይልቅ ፈርቶ በሸሸ ነበር።

ዳዊት ወደ ጎልያድ በቀረበ ጊዜ እንዲህ ይለዋል፤ «አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለና፤ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርከው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም <u>በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ</u>። እግዚአብሔርም ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፤ እመታህማለሁ ራስህንም ከአንተ አነሣዋለሁ የፍልስጥኤማውያንንም ሠራዊት ሬሶች ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ።» የዳዊት መሣሪያ የእግዚአብሔር ስም ነበር። (ቁ. 45-46)

«የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል።» ምሳሌ 18፥10 ስለዚህ ነው፣ ዳዊት በመዝሙር 20፥7-8 «እነዚያ በሰረገላ እነዚያ በፈረስ ይታመናሉ፤ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን። እነርሱም ተሰነካከለው ወደቁ፣ እኛ ግን ተነሣን ጸንተንም ቆምን።» በማለት የዘመረው። እንዲሁም በመዝ. 118፥10-12 «አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኋቸው መክበቡንስ ከበቡኝ በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኋቸው ።» ይላል።

ዳዊት፣ እስራኤላወያንና ፍልስጥኤማውያን ተፋጥጠው በነበሩበት የሰልፍ ቦታ የሄደው ለውጊያ ሳይሆን አባቱ እሴይ ለታላቅ ወንድሞች ምግብ ይዞ እንዲሄድና ደኅንነታቸውን እንዲጠይቅ ስለላከው ነበር። እግዚአብሔር ግን ለዳዊት ሌላ ሰማያዊ ተልእኮ ነበረው። ያም ተልእኮ የጎልያድን ተግዳሮት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለማራቅ ነበር። ምናልባት በምንሠራበት ቦታ ወይም ያለ ፈቃዳችን እንድንቀመጥ በተደረግንበት ቦታ ከሰዎች የተቀበልነውን ተልዕኮ ብቻ እናይ ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ሌላ ሰማያዊ ተልዕኮ አለው።

ዳዊት አባቱ ልኮት ወደ ሰልፉ ከሄደ በኋላ ታላቅ ወንድሙ ኤልያብ አይቶት እንደተቆጣው እናያለን፡ - «ለምን ወደዚህ ወረድህ? እነዚያንስ ጥቂት በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው? እኔ ኩራትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል አለው፡፡» የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ እያደረግን ተቃውሞ ሊደርስብን ይችላል፤ ያውም ከወንድሞቻችን፡፡ «ዳዊትም፡- እኔ ምን አደረግሁ? ይህ ታላቅ ነገር አይደለምን? አለ፡፡ ዳዊት ከእርሱ ወደሌላ ሰው ዘወር አለ፡፡» ተቃውሞ ሊደርስብን ይችላል ያውም ከወንድሞቻችን ከእግዚአብሔር ተልእኮና ዓላማ ሊያደናቅፈን አይገባም፡፡ ነገር ግን ከዚያ ተቃውሞ «ዘወር» ማለት አለብን፡፡ ያለ ተቃውሞ የእግዚአብሔርን ተልእኮ መፈጸም አንችልም፡፡

ዳዊት በሳዖል ፊት ቀርቦ፤ «ስለ እርሱ (ስለ ጎልያድ) የማንም ልብ አይውደቅ፤ እኔ ባሪያህ ሄጄ ያንን ፍልስጥኤማዊ እወጋዋለሁ አለው፡፡» በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ጠላትን የሚዋጋ ሰው ሲጠፋ የእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ይወድቃል፡፡ ነገር ግን አንዱ የእምነት ጀግና ተነሥቶ በእግዚአብሔር ስም በሚዋጋበት ጊዜ ልቡ የወደቀበት ሁሉ እልል ማለት ይጀምራል፡፡ «የእስራኤልና የይሁዳ ሰዎች ተነሥተው እልል አሉ ፍልስጥኤማውያንንም እስከ ጌትና እስከ አስቀሎና በር ድረስ አሳደዱአቸው፡፡»

ዳዊት ጎልያድን ያሸነፈው ያቺን ድንጋይ በወነጨፈ ጊዜ ሳይሆን፤ በእረኝነት እያለ የአንበሳ ደቦል መጥቶ ከመንጋው ጠቦት ሊወስድ ሲል መትቶ ባስጣለውና በገደለው ጊዜ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ዓይን ያን ጊዜ ነበር ጐልያድን ያሸነፈው፡፡ መንጋዬ የሆነው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመንጠቅ ሊመጣ ያለውን የሰው አንበሳ (ጎልያድን) እንደዚሁ የሚጥልልኝ ባሪያዬን አገኘሁ ሳይል አይቀርም፡፡ መዝ 89÷20-23

«ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት

ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት

እጄም ትረዳዋለች

ክንዴም ታጸናዋለች

ጠላት በእርሱ ላይ አይጠቀምም...»

ዳዊት ጎልያድን ለመዋጋት ሲሄድ ሳዖል የራሱን ልብስ ሊያለብሰው ሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ውጊያ የምንዋጋው እግዚአብሔር በግል ያለበሰንን ልብስ ለብሰን እንጂ የሳዖልን ልብስ ተውሰን ስላልሆነ፣ «ዳዊት ሳዖልን፡ - አልፈተንሁትምና እንዲህ ብዬ መሄድ አልችልም አለው፡፡ ዳዊትም አወለቀ፡፡» ሰዎች ያለበሱንን አውልቀን እግዚአብሔር ያለበሰንን መልበስ አለብን፡፡ «በትሩንም በእጁ ወሰደ፣ ከወንዝም አምስት ድብልብል ድንጋዮች <u>መረጠ</u>፣ በእረኛ ኮረጆውም በኪሱ ከተታቸው፤ ወንጭፍም በእጁ ነበር፣ ወደ ፍልስጥኤማዊውም ቀረበ፡፡» በእረኝነቱ ጊዜ አንበሳውንና ድቡን ሲገድል የጦር መሣሪያ፣ ሰይፍና ቀስት ይዞ አልነበረም ድልን ያገኘው፡፡ ጎልያድ ከአንበሳና ከድብ ስለማይበልጥ ልዩ ትጥቅ አላስፈለገውም፡፡ «በዳዊት እጅ ሰይፍ አልነበረም» (ቁ. 50)

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት
<u>የዳዊትና የዮናታን ፍቅር፤ የሳዖል ቅንዓት</u>

«ዳዊትም ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፣ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው» ዳዊትና ዮናታን አንድ ዓይነት ልብ ነበራቸው፤ ሁለቱም እግዚአብሔርን በመታመን ጠላትን ድል ያደረጉና የእስራኤልን ሕዝብ ያዳኑ ሰዎች ናቸው።

ዮናታን በምዕ. 14÷6 «ና ወደ እነዚህ ቈላፋን ጭፍራ እንለፍ በብዙ ወይም በጥቂት ማዳን እግዚአብሔርን አያስቸግረውምና» እንዳለ እናነባለን፤

በምዕ. 17÷26 ደግሞ ዳዊት፤ «... የሕያውን አምላክ ጭፍሮች የሚገዳደር ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ማን ነው?» ይላል። ሁለቱም ጠላታቸውን ያዩት ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አንጻር ነበር። ሁለቱም የእምነት እርምጃ ወሰዱ፤ ሁለቱም ታላቅ ድልን ለእግዚአብሔር ሕዝብ አስገኙ።

የዳዊትንና የዮናታንን መዋደድ በምናይበት ጊዜ እግዚአብሔር በሳኦል በኩል በዳዊት ላይ የሚመጣበትን ታላቅ ስደት ስለሚያውቅ ያዘጋጀለት መውጫ መንገድ ይመስላል። «ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያዘጋጃል» ተብሎ እንደተጻፈ፤ ዮናታን ለዳዊት በተደጋጋሚ ከሳኦል የሚድንበት መንገድ ሲሆነው እናያለን። ከዚህ የምንማረው፤ ሰይጣን ምንም ዓይነት ስደትና መከራ ቢያስነሳብንም እግዚአብሔር አስቀድሞ (ስደቱና መከራው ገና ሳይጀምር) ከስደቱና ከመከራው የምንከለልበትን ወይም በስደቱና በመከራው ውስጥ የምናልፍበትን መንገድ እንደሚያዘጋጅልን ነው።

ዳዊት ጎልያድን ከገደለ በኋላ፣ ሴቶች እየዘፈኑ «ሳኦል ሺህ፣ ዳዊትም እልፍ ገደለ» ሲሉ ሳኦል ስለሰማ፤ «ከዚያ ቀን ጀምሮ ሳኦል ዳዊትን ተመቅኝቶ ተመለከተው።» (ቁ. 9) እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነት ሙገሳ ይጠብቀን ከእግዚአብሔር የሆነ ምሥጋና መንፈስን ያበረታታል፤ ከሥጋና ከደም የሆነ ምሥጋና ወይም ሙገሳ ግን ችግር ውስጥ ይከታል።

«በነጋውም ሳኦልን ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያዘው፤ በቤቱም ውስጥ ትንቢት ተናገረ።» (ቁ. 10) ሳኦል ዳዊትን ተመቅኝቶ መመልከት በጀመረበት ማግስት ክፉ መንፈስ እንደያዘው እናያለን። ምቀኝነትና ቅንአት ለክፉ መንፈስ በር እንደሚከፍት ማስጠንቀቂያ ታሪክ ነው።

«በቤቱም ውስጥ ትንቢት ተናገረ» ሲል፣ ትንቢት በክፉ መንፈስ አነሳሽነት ሊነገርም እንደሚችል ያሳያል። በአዲስ ኪዳን «መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ (ዮሐ. 4÷1) የሚለን፣ በክፉ መናፍስት የሚሠሩ ብዙ መልካም ወይም እውነተኛ የሚመስሉ ነገሮች ስላሉ ነው። እንዲሁም በ1ቆሮ. 14÷29 «ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው።» ይላል ይለዩአቸው የሚለው ቃል «ከእግዚአብሔር እንደሆነ መርምሩ» ከሚለው ሐሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ሳኦል በ 1ሳሙ. 10÷10 «... የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት በመካከላቸው ትንቢት ተናገረ።» ይላል በ1ሳሙ. 18÷10 ደግሞ፣... ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያዘው በቤቱም ውስጥ ትንቢት ተናገረ።» ይላል። ያው ሰው በተለያዩ ጊዜያት ለቅዱስ መንፈስና ለርኩስ መንፈስ ሲገዛ ማየት እንችላለን። የክፉ መንፈስ መጠቀሚያ ከመሆን እግዚአብሔር ይጠብቀን።

ሳኦል በዳዊት ላይ ምንም ቢነሣና ሊያጠፋው ቢሞክር፤ «እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ፣ ከሳኦልም ስለተለየ ሳኦል ዳዊትን ፈራው። ዳዊትም በአካሄዱ ሁሉ አስተውሎ ያደርግ ነበር።» (ቁ. 12-14) «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?» (ሮሜ 8÷31)

ሳዖል ፊት ለፊት ጦር ወርውሮ ዳዊትን መግደል ሳይሆንለት ሲቀር፤ በስውር ወዳጅ መስሎ፣ ልጄን እድርልሃለሁ ብሎ ሊያስገድለው ሲሞክር እናያለን። «ሳዖልም ባሪያዎቹን፡ - እነሆ፣ ንጉሥ እጅግ ወዶሃል ባሪያዎቹም ሁሉ ወድደውሃል፣ አሁንም ለንጉሥ አማች ሁን ብላችሁ በስውር ለዳዊት ንገሩት ብሎ አዘዛቸው።» (ቁ. 22)

«ሳኦልም ዳዊትን በፍልስጥኤማውያን እጅ ይጥለው ዘንድ አስቦ፡ - የንጉሥን ጠላቶች ይበቀል ዘንድ ከመቶ ፍልስጥኤማውያን ሸለፈት በስተቀር ንጉሥ ማጫ አይሻም ብላችሁ ለዳዊት ንገሩት አላቸው።» (ቁ. 22)

ሰይጣንም፣ ፊት ለፊት ተዋግቶን ሲያቅተው ወዳጅ መስሎ በውሸት ፍቅር ይመጣል። የእግዚአብሔር ቃል፤ «እባብና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፤ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ።» (ሉቃ. 10፥19) እባብ፡- ፊት ለፊት የሚናደፍ ጠላት ሲሆን፤ ጊንጥ፡- ደግሞ በጅራቱ በጀርባ፣ (በስውር) የሚናደፍ ጠላት ነው።

«ዳዊትና ሰዎቹም ተነሥተው ሄዱ ከፍልጥኤማውያንም መቶ ሰዎች ገደሉ፤ ዳዊት ለንጉሥ አማች ይሆን ዘንድ ሰለባቸውን አምጥቶ በቁጥራቸው ልክ ለንጉሡ ሰጠ። ሳዖልም ልጁን ሜልኮልን ዳረለት። ሳዖልም እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደሆነ አየ፤ እስራኤልም ሁሉ ወደዱት።» ቁ 28

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ጠላቶቻችን፣ የሚመቀኙን፣ በፊት ለፊትም ሆነ በስውር የሚዋጉን ሁሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሆነ ያያሉ።

## <u>ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ</u>

### <u>ሳዖል ዳዊትን ማሳደድ ይቀጥላል፤ ዮናታንና ሚልኮል ዳዊትን ይረዳሉ።</u>

ዮናታን ለአባቱ ለሳዖል «… ስለ ዳዊት መልካም ተናገረ። ሳዖልም የዮናታንን ቃል ሰማ።» ቁ. 5-6 በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚያስፈልጉን ስለሌላው «መልካም የሚናገሩ» ናቸው። ክፉን፣ ጉድለትን፣ ድካምን ስለሌላው የሚናገሩ ብዙ አሉ፤ የእግዚአብሔርን ቤት የሚያፈርሰውም እንዲህ ዓይነቱ ወሬ ነው። ነገር ግን ስለ ማንም ቢሆን ከዲያብሎስ በስተቀር መልካም የሆነውን ብቻ ማውራት መልካም ነው።

ሳዖል፤ ምንም ለጊዜው ልቡ ወደ ዳዊት ቢመለስም ክፉ መንፈስ የሚነዳው ሰው ስለነበር፣ ወዲያውኑ ተለውጦ ዳዊትን ለመግደል ይነሣ ነበር። ዮናታንና ሜልኮል ምንም የሳዖል ልጆች ቢሆኑ እግዚአብሔር በፊታቸው በዳዊት ሞገስን ሰጥቶት ስለነበር፣ ከአባታቸው እጅ ሲያድኑት እናያለን።

ቁ. 18 «ዳዊትም ሸሽቶ አመለጠ ወደ አርማቴምም ወደ ሳሙኤል መጣ፣ ሳዖል ያደረገበትን ሁሉ ነገረው እርሱና ሳሙኤልም ሄዱ በዋትዘራምም ተቀመጡ።»

ዳዊት ከሳዖል ሲሸሽ ወደ ሳሙኤል ግን ሲጠጋ እናያለን። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስንመላለስ ቅባታችንን ከእኛ ለመውሰድና አካሄዳችንን ለማሰናከል እንዲሁም የእግዚአብሔር ዓላማ በሕይወታችን እንዳይፈጸም የሚዋጋ የሳዖል መንፈስ ሊኖር ይችላል፤ እኛ ማድረግ ያለብን ከእንደዚህ ዓይነቱ መንፈስ እየራቅን የእግዚአብሔር ቅባት ወዳለባቸው ሳሙኤሎች መቅረብና ሁኔታችንን ለእነርሱ መግለጽ ነው። መፍትሔ በእውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ውስጥ አለ።

ሳዖል፣ ዳዊት ወደ ሳሙኤል እንደሄደ ሲሰማ ይዘው እንዲያመጡት መልእክተኞችን ላከ። ዳዊት የተተገነባት ከተማ ሳሙኤልና የነቢያት ጉባኤ የነበሩባት ስለነበረች፣ እነዚህ መልእክተኞ ሲመጡ፣ የነቢያት ጉባኤ ትንቢት ሲናገሩ፣ ሳሙኤልም አለቃቸው ሆኖ ሲቆም ባዩ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በሳዖል መልእክተኞች ላይ ወረደ እነርሱም ትንቢት ይናገሩ ጀመር። ሳዖልም ያንን በሰማ ጊዜ ሌሎች መልእክተኞችን ሰደደ እነርሱም ደግሞ ትንቢት ተናገሩ፣ እንደገናም ሦስተኛ ጊዜ መልእክተኞችን ሰደደ እነርሱም ደግሞ ትንቢት ተናገሩ።» ቁ. 20-21

ሰይጣን የፈለገውን ዓይነት መልእክት ደጋግሞ ቢልክብን እኛ ማድረግ ያለብን የእግዚአብሔርን ቃል መናገር ነው። እኛ የእግዚአብሔርን ቃል ስንናገር መልእክተኞቹ በእግዚአብሔር ቃል ይማረካሉ ተልእኮአቸውንም መፈጸም አይችሉም። በጠላት መልእክት ወይም ቃል ከመርበድበድ የእግዚአብሔር መንፈስ በልባችን ያስቀመጠውን ቃል በመናገር ጠ ላትን ማርበድበድ ይሻላል።

በመጨረሻም ሳዖል ራሱ ተቆጥቶ ዳዊት ወዳለበት መጣ። «የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ደግሞ ወረደ ወደ ነዋትዘራም እስኪመጣ ድረስ ትንቢት ይናገር ነበር … ራቁቱንም ወድቆ በዚያን ሌሊት ሁሉ ተጋደመ።» የእግዚአብሔር መንፈስ አመጸኛውን ከቁጥጥር ሥር ሲያደርግ እናያለን። የእግዚአብሔር መንፈስ የወረደበት ለበረከት ሳይሆን አንድ ወንጀለኛ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንደሚውል መንፈስ ቅዱስ ሊያጋድመው ፈልጎ ነው።

እኛም በጠላት ተቃውሞ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ከተናገርን፤ «የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጣል።» (ሮሜ 16÷20) የሚል ጽኑ ተስፋ አለን።

<u>*ምዕራፍ ሃያ*</u>

<u>*ዳዊትና ዮናታን እንደገና ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፤*</u>

ዮናታን የሳዖል ሐሳብ ምን እንደሆነ ከተረዳ በኋላ ለዳዊት እንደሚነግረው ቃል ይገባለታል። በገባለትም ቃል መሠረት ሳዖል ሊገድለው እንደሚፈልግ ለዳዊት ከነገረው በኋላ ተላቅሰውና ተሳስመው ይለያያሉ።

ዮናታን ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን መግባት ብቻ ሳይሆን ዳዊት ያልፍበት የነበረውንም መከራ እንደተካፈለ እናያለን።

ቁ. 30 «የሳዖልም ቁጣ በዮናታን ላይ ነደደ፤»

(ቁ. 32-33) «ዮናታንም ለአባቱ ለሳዖል፡- ስለምን (ዳዊት) ይሞታል? ያደረገውስ ምንድር ነው? ብሎ መለሰለት። ሳዖልም ሊወጋው ጦሩን ወረወረበት» ዮናታን፣ በዳዊት ላይ የነበረውን የአባቱን ቁጣና የቀስት ውርወራ ተካፋይ ሆነ። <u>«ዮናታን ስለ ዳዊት እጅግ አዝኖአልና</u> እጅግ ተቆጥቶ ከሰደቃው ተነሣ።» ቁ. 34 ይህ ምዕራፍ የእውነተኛ ቃል ኪዳንን ትርጉም የሚያሳይ ምዕራፍ ነው። በሁለት ሰዎች ወይም አካሎች መካከል ቃል ኪዳን በሚደረግበት ጊዜ በአንዱ ላይ የሚደርሰው መከራም ሆነ ደስታ በሁለቱም ላይ እንደደረሰ አድርጎ ማየት ማለት ነው። ዮናታን የንጉሥ ልጅ ሆኖ ሳለ የራሱ ምንም ችግርና መከራ ሳይኖርበት ዳዊትን ስለወደደ ብቻ ከአንድ በመሰደድ ላይ ካለ ሰው ከዳዊት ጋር ቃል ኪዳን ሲገባ እናያለን። በዳዊት ላይ በመወርወር ላይ ያለው ስድብና ፍላፃ ሁሉ ተካፋይ ሲሆን እናያለን። የደስታውና የድሉም ተካፋይ እንደሚሆን የገቡት ቃል ኪዳን ያመለክታል።

ቁ. 15 «እግዚአብሔር የዳዊትን ጠላቶች ሁሉ እያንዳንዱ ከምድር ባጠፋቸው ጊዜ ለዘላለም ቸርነትህን ከቤቴ አታርቀው» ከዚህ ምዕራፍ ስለ እውነተኛ ቃል ኪዳን የምንማረው፤

1. እውነተኛ ቃል ኪዳን በግል ጥቅም ላይ ሳይሆን በፍቅር ላይ የተመሠረተ እንደሆነ።
2. እውነተኛ ቃል ኪዳን መከራንም ሆነ ደስታን አብሮ መካፈል እንደሆነ።
3. በእውነተኛ ቃል ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር እንደሚኖርና ያንን ቃል ኪዳን እንደሚያጸና።

(ቁ. 42) «ዮናታንም ዳዊትን በደኅና ሂድ እነሆ ሁለታችን፣ በእኔና በአንተ፣ በዘሬና በዘርህ መካከል ለዘላለም እግዚአብሔር ይሁን ብለን በእግዚአብሔር ስም ተማምለናል አለው።»

ዳዊት ለዮናታን የገባውን ቃል ኪዳን ዮናታን ከሞተ በኋላ ለልጁ ሲፈጽምለት በ2ሳሙ. ምዕ. 9 እናያለን።

<u>ምዕ. 21-22</u> ዳዊት ከሳዖል ለመሸሽ ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንደሄደ፤ በእርሱ ምክንያት ሳዖል 85 ካህናትን እንዳስገደለና 400 የሚሆኑ ሰዎች ዳዊትን መከተል እንደጀመሩ።

ምዕ. 21÷1-9 ዳዊት ወደ ካህኑ ወደ አቤሜሌክ እንደመጣና ካህናት ብቻ እንዲበሉ የተፈቀደውን የተቀደሰ እንጀራ እንደሰጠው እንዲሁም አስቀምጦት የነበረውን የጎልያድን ሠይፍ እንደሰጠው እናያለን። ይህንን ሁሉ ሲያደርግ ዳዊት ከሳዖል ኮብልሎ እንደመጣ አላወቀም ነበር። በወንጌል ውስጥ ጌታ የሱስ ይህንን ክፍል ጠቅሶ አላነበባችሁምን? ሲላቸው እናያለን (ሉቃ. 6÷3-4)።

ምዕ. 21÷10-15 ዳዊት ወደ ጌት ንጉሥ ወደ አንኩስ ሲሄድ፣ ነገር ግን የአንኩስ ባሪያዎች «ይህ ዳዊት የአገሩ ንጉሥ አይደለምን?» ብለው ጥያቄ ስላቀረቡ፣ ዳዊት ንጉሡ እንዳይገድለው ስለፈራ ዕብድ መስሎ በንጉሡ ፊት በመንፈራፈር ከጉድ ሲያመልጥ እናነባለን። መዝሙረ 55 (56)ትን የዘመረው በዚህ ጊዜ ነው። የሚገርመው ነገር፣ ዳዊት የኮበለለበት አገር በምዕ 17 የገደለው የጎልያድ አገር ነበር። ።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደ ሳዖል ያለ በክፉ መንፈስ የሚነዳ ሰው ሲሰለጥን የእግዚአብሔር ሰዎች ወደ አሕዛብ መኮብለል ይጀምራሉ። ኢየሱስ በህፃንነቱ ሔሮድስን ሸሽቶ ወደ ግብጽ እንደ ተወሰደ በወንጌል እናነባለን።

በምዕ. 22÷1-2 ዳዊትን፣ በመጀመሪያ ቤተሰቡ በኋላም የተጨነቁ፣ ብድር የነበረባቸው፣ የተከፉ ሰዎች መጥተው በላያቸው አለቃ እንዳደረጉት እናነባለን ከነዚህ ሁለት ጥቅሶች የምንማረው፤

1. በፊት ከቁጥር እንኳን ያላስገቡት ቤተሰቡ አለቃቸው እንዲሆን ወደዱ። ሳሙኤል ሊቀባው ሲመጣ እሴይ ከልጆቹ መካከል እንኳን አላቀረበውም ነበር። እንዲሁም በምዕ. 17 ላይ ወንድሙ ኤልያብ ለምን ወደ ጦር ሰፈር መጣህ ብሎ ሲቆጣው እናያለን። አሁን ግን በእግዚአብሔር ሞገስ የቤተሰቡ አለቃ ሆነ።

2. ከቤተሰቡ ቀጥሎ አለቃ የሆነባቸው ሰዎች የተጨነቁ፣ ዕዳ የነበረባቸውና የተከፉ ሰዎች እንደነበሩ እናነባለን። ዳዊት የተቀባው በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ እንዲሆን ነበረ። ነገር ግን አለቅነቱ የጀመረው ከኅብረተሰቡ ከተገፉና ከተናቁ ሰዎች ነበር። እግዚአብሔር ለአንድ ኃላፊነት በሚቀባን ጊዜ፣ የሚያስጀምረን ከታች፣ ዝቅ ካለው ደረጃ እንጂ ከላይ አይደለም። የእግዚአብሔር አላማ ከታች ወደላይ እንድናድግ እንጂ ከላይ እንድንጀምር አይደለም።

ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ የሆነው፣ በመጀመሪያ በእነዚህ ሰዎች ላይ አለቃ በመሆን በኋላም ሳዖል ሲሞት በኬብሮን ለሰባት ዓመታት ከነገሠ በኋላ ነው።

3. ቁ. 3-5 ዳዊት ወደ ሞዓብ ንጉሥ ይመጣና አባቱና እናቱ በሞዓብ ምድር እንዲቀመጡ ይጠይቀዋል። ሞዓብ በተለያዩ ጊዜያት እስራኤልን የወጋ የእሥራኤል ጠላት እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል እንረዳለን ለዳዊት ግን እግዚአብሔር በጠላት ፊት እንኳን ሞገስን ሰጥቶት ነበር። «የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደሆነ በእርሱና በጠላቶቹ መካከል ስንኳ ሰላምን ያደርጋል።» ምሳ. 16÷7 ከቁ. 6-23 ዳዊት ለካህኑ ለአቤሜሌክ ምግብና ሰይፍ ስጠኝ ብሎ ሲቀበል ያይ የነበረ አንድ ዶይቅ የሚባል ሰባቂ ለሳዖል ስለተናገረ ሳዖል ካህኑ አቤሜሌክንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ካህናት ሁሉ አስጠርቶ «አንተና የእሴይ ልጅ ለምን ዶለታችሁብኝ? እንጀራና ሰይፍ ሰጠኸው፣ ዛሬም እንደተደረገው ጠላት ሆኖ ይነሣብኝ ዘንድ እግዚአብሔርን ስለ እርሱ ጠየቅህለት» ይለዋል (ቁ. 13)። በኋላም አቤሜሌክንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ካህናት እንዲገድሏቸው ባሪያዎቹን ያዛቸዋል፤ «የንጉሡ ባሪያዎች ግን እጃቸውን በእግዚአብሔር ካህናት ላይ ይዘረጉ ዘንድ እንቢ አሉ።» ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ በየትም ቦታ ቢሆን ከሰዎች ሥልጣን ሥር ሆነን ስንሠራ፣ እነርሱን መታዘዝ ያለብን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ኅሊናችንን እስካልነካ ድረስ ብቻ መሆን አለበት። ኅሊናችንን ሸጠን ማንንም መታዘዝ የለብንም።

የንጉሡ ባሪያዎች እንቢ ባሉ ጊዜ ሳዖል በመጀመሪያውኑ ያሳበቀውን ኤዶማዊውን ዶይቅ «አንተ ዞረህ በካህናቱ ላይ ውደቅባቸው» ይለዋል። ዶይቅም 85 የሚሆኑ ካህናትን በዚያ ቀን ገደለ ይህን ሰው ደም አስክሮት ስለነበረ፣ ወደ ካህናቱ ከተማ ሄዶ በከተማው ያሉትን ህፃናትንና ጡት የሚጠቡትን ሳያስቀር እንስሳትንም ሁሉ አጠፋ።

ስለዚህ አመፀኛ ሰው ዳዊት በመዝ. 52 ላይ ሲቀኝ እናነባለን።

ዶይቅ ካህናቱን ሁሉ በጨረሰ ዕለት ከአቤሜሌክ ልጆች አንዱ ብቻ አምልጦ ወደ ዳዊት ሸሸ። ስሙም አብያታር ይባል ነበር። ለዳዊት ካህን ሆኖ ለብዙ ዘመናት አገለገለ።

ምዕ. 23 ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጋ፤ ከሳዖል ደግሞ ሲሸሽ፤

ከቁ. 1-5 ዳዊት ፍልስጥኤሞቿያንን ልምታን? ብሎ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ እግዚአብሔር «ሂድ ፍልስጥኤማውያንን ምታ ቅዒላንም አድን አለው።» ከዳዊት ጋር አብረው የነበሩት ሰዎች ግን ፈርተው፤ «እነሆ በዚህ በይሁዳ መቀመጥ እንፈራለን፣ ይልቁንስ በፍልስጥኤማውያን ጭፍሮች ላይ ወደ ቅዒላ ብንሄድ እንዴት ነው? አሉት» (ቁ. 3)

ዳዊትን ተከትለው የነበሩት ሰዎች በጦር ስልት የሠለጠኑ ሳይሆኑ፤ በምዕ 22 እንዳየናቸው የተጨነቁ፣ ብድር የነበረባቸው፣ የተከፉ ስለነበሩ ሆ! ብለው አለቃቸውን ተከትለው ወደ ጦር ሜዳ የሚሄዱ አልነበሩም። ዳዊት የእግዚአብሔርን ድምፅ ቢሰማም አብረውት የነበሩትን ሰዎች ፍርሃትና ስሜት ቸል ሳይል ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ እናነባለን። (ቁ. 4) ከዚህ ሁኔታ የምንማረው፤ እኛ አንድ ነገር ተገልጾልናል፣ ተረድተናል ብለን አብረውን ያሉትን ሰዎች ስሜትና ሐሳብ ቸል ብለን በእኛ ሥር ያሉትን ሰዎች እንደ ከብት መንዳት እንደሌለብን ነው። ሁለተኛ ጊዜ የጠየቀው ለራሱ ሳይሆን ለተከታዮቹም ጭምር ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ሲመልስለት አብረውት ያሉትም ተስማምተው እንደሄዱና እንደ ተዋጉ ድልንም እንዳገኙ እናያለን። ዳዊት፤ የሚከተሉት ከእርሱ ጋር አንድ ልብ እስከሚሆኑ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት ቀረበ።

ከቊ. 6-29 ዳዊት ከሳዖል ሲሸሽና እግዚአብሔር ሲጠብቀው እናያለን። በቁ. 7 ላይ ሳዖል «እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ ሰጥቶታል» ሲል እናነባለን። የሚሠራው የሰይጣንን ሥራ ሆኖ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረገ ይመስል የእግዚአብሔርን ስም ይጠራል። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርት «የሚገድላችሁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ይመስለዋል» እንዳላቸው። ሳዖል ዳዊትን ያላገኘው በዳዊት ቅልጥፍና ሳይሆን የእግዚአብሔር ጥበቃ በእርሱ ላይ ስለነበረ እንደሆነ እናያለን።

ቁ. 14 «... ሳዖልም ሁልጊዜ ይፈልገው ነበር <u>እግዚአብሔር ግን</u> በእጁ አሳልፎ አልሰጠ ውም።» ከጠላት ፍላፃና ወጥመድ ሁሉ ተጠብቀን በሰላም ወተተን የምንገባው በእግዚአብሔር ጥበቃ ብቻ ነው። «ሳዖልም በተራራው በአንድ ወገን ሄደ ዳዊትና ሰዎቹም በተራራው በሌላው ወገን ሄዱ። ሳዖልና ሰዎቹም ዳዊትንና ሰዎቹን ለመያዝ ከብበዋቸው ነበርና ዳዊት ከሳዖል ፊት ያመልጥ ዘንድ ፈጠነ። ወደ ሳዖልም መልእክተኛ መጥቶ ፍልስጥኤማውያን አገሩን ወርረውታልና ፈጥነህ ና አለው። ሳዖልም ዳዊትን ማሳደድ ትቶ ተመለሰ ከፍልስጥኤማውያንም ጋር ሊዋጋ ሄደ።» ቁ. 26-28 ዳዊት «ያመልጥ ዘንድ ቢፈጥንም» ያመለጠው በእግዚአብሔር ጥበቃ እንጂ በእርሱ መፍጠን አልነበረም።

በአጠቃላይ፤ ከዚህ ምዕራፍ የምናየው በጣም የሚገርም ነገር፤ ከቁ. 1-5 ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ሲዋጋ እናያለን በቁ. 28 ደግሞ ሳዖል ፍልስጥኤማውያንን ሲዋጋ እናያለን፣ በሁለቱ ቁጥሮች መካከል ግን ሳዖል ዳዊትን ሲያሳድድ (ሲዋጋ) እናያለን። የሁለቱም ጠላቶች ፍልስጥኤማውያን ነበሩ፣ እርስ በርስ ግን በአንድነት ሆነው የጋራ ጠላታቸውን ሲዋጉ አናይም። መሪዎች ሲስቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ እርስ በርሱ አንደ ጠላት መተያየት ይጀምራል። ጠ ላትን በመውጋት ከሚያጠፋው ጊዜና ኃይል ይልቅ እርስ በርስ በመዋጋት የሚጠፋው ጊዜና ኃይል ይበልጣል።

*<u>ምዕራፍ ሃያ አራት</u>*:

*ዳዊት ሳዖልን በሰይፉ ሳይሆን በኀሊና ውጊያ ሲያሸንፈው እናያለን።*

ዳዊት ግዙፍ የነበረውን ጎልያድን በአንዲት ጠጠር ዘርሮ በእግዚአብሔር ስምና እርዳታ ሲያሸንፈው በምዕራፍ 17 አይተናል። ሳዖልን ግን በሰይፍና በወንጭፍ እንዲዋጋውና እንዲያሸንፈው የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልነበረ ዳዊት ሳዖልን በሰይፍ ገድሎ ሊያሸንፈው በሚችልበት ቅጽበት እንኳን፣ አብረውት የነበሩት ሰዎችም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል ግደለው ሲሉት፤ «እግዚአብሔር በቀባው በጌታዬ ላይ እንዲህ ያለውን ነገር አደርግ ዘንድ እጄንም እጥልበት ዘንድ እግዚአብሐር ከእኔ ያርቀው» አላቸው።

ሳዖል በዋሻ ውስጥ ገብቶ ሲፀዳዳ ዳዊትና ሰዎቹ በውስጠኛው ክፍል ስለነበሩ፣ ዳዊት የሳዖልን መጎናጸፊያ ዘርፍ በቀስታ በቆረጠ ጊዜ የዳዊት ልብ በኀዘን ተመታ። ሳዖልም ተጸዳድቶ ከዋሻ ከወጣ በኋላ ዳዊት ተከትሎ በመውጣት ሳዖልን «እነሆ ዛሬ በዋሻው ውስጥ እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ እንደ ሰጠህ ዓይንህ አይታለች፣ አንተንም እንድገልህ ሰዎች ተናገሩኝ፤ እኔ ግን፡ - በእግዚአብሔር የተቀባ ነውና <u>እጄን በጌታዬ ላይ አልዘረጋም</u> ብዬ <u>ራራሁልህ</u> ... የልብስህ ዘርፍ በእጄ እንዳለ ተመልክተህ እወቅ ... <u>እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካከል ይፍረድ</u>፣ <u>እግዚአብሔርም አንተን ይበቀልልኝ</u>፣ እጄ ግን በአንተ ላይ አትሆንም» በማለት ዳዊት በርኅራኄ በትኅትና በቀልንና ፍርድን ደግሞ ለእግዚአብሔር በመስጠት ሳዖልን ሲያሸንፈው እናያለን።

«ሳዖልም ድምፁን ከፍ አድርጎ አለቀሰ። ዳዊትን አለው፡- እኔ ክፉ በመለስኩብህ ፈንታ በጎ መልሰህልኛልና አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ። ... ለእኔ ስላደረግኸው ቸርነት

እግዚአብሔር ይመልስልህ» ይለዋል። የተመረጡ ሦስት ሺህ ሰዎች ይዞ እንደ ቆቅ አድኖ ሊገድለው የነበረውን ሰው እያለቀሰ «እግዚአብሔር ይመልስልህ» እንዲል ያደረገው የዳዊት የሰይፍ ውጊያ ሳይሆን የኀሊና (የትህትና፣ የርኅራኄና እግዚአብሔርን የመፍራት) ውጊያ ነበር። ከዚህ ምዕራፍ የምናየው ዳዊት በብሉይ ኪዳን ዘመን በአዲስ ኪዳን መመሪያ ይኖር የነበረ ሰው እንደነበረ ነው። በሮሜ 12፥14-21 ያለውን ክፍል ብናነብ በዚህ ምዕራፍ ዳዊት በተግባር ያደረገውን ድርጊት ጳውሎስ ለክርስቲያኖች በምክር መልክ ይናገራል።

- ❖ የሚያሳድዷችሁን መርቁ
- ❖ የትህትናን ነገር ለመሥራት ትጉ
- ❖ ለማንም በክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ
- ❖ ለራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ
- ❖ ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አትሸነፉ

ዳዊት እነዚህ ምክሮች በአዲስ ኪዳን ከመሰጠታቸው ከ1000 ዓመታት በፊት በተግባር ሲፈጽማቸው እናያለን። ይህ ምዕራፍ ለእኛ የሚሰጠን ትምህርት፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል አለመግባባት ቢነሣ አንዱ በሌላው ላይ ሰይፍና ፍላፃ ይዞ መዋጋት ሳይሆን እንድንዋጋበት የሰጠን መሣሪያዎች

1. ርኅራኄ
2. ትህትና
3. በቀልንና ፍርድን ለእግዚአብሔር መተው
4. ክፉውን በመልካም ማሸነፍ ናቸው።

ይህም በአጠቃላይ የኀሊና ውጊያ ይባላል።

ዳዊት በዋሻ ውስጥ አግኝቶ በሰይፍ ቢገድለው ኖሮ አሁን ካደረገው የበለጠ አያሸንፈውም ነበር፣ እንደውም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሚሆን ውጊያ ስለሚሆን የዕድሜ ልክ ጸጸት ይሆንበት ነበር።

በእግዚአብሔር ቤት ብዙ ጊዜ የሚታየው ውጊያ በዚህ ምዕራፍ እንደምናየው ክፉውን በመልካም ማሸነፍ ሳይሆን ክፉን በክፉ ለማሸነፍ መሞከርና ሁለቱም ተሸናፊዎች የመሆን ሁኔታ ነው።

## ምዕራፍ ሃያ አምስት

አቢግያ ዳዊትን ከበቀልና በከንቱ ደም ከማፍሰስ እንደጠበቀችው።

የአቢግያ ባል ናባል ባለጸጋ ሰው ቢሆንም ባለጌ፣ ሰነፍና ምናምንቴ ሰው እንደነበረ እናነባለን። አቢግያ ግን በአንፃሩ፣ አስተዋይ፣ ትጉህና ትሁት ሴት ነበረች።

ዳዊት የናባልን መንጋ የሚጠብቁትን ብላቴናዎች አክብሮና ለእነርሱ ሌትና ቀን እንደ አጥር ሆኖ መልካምን ካደረገለት በኋላ፣ ናባል በጎቹን በሚሸልትበት ጊዜ «በመልካም ቀን መጥተንብሃልና ጎልማሶች በፊትህ ሞገስ ያግኙ፣ በእጅህም ከተገኘው ለባሪያዎችህና ለልጅህ ለዳዊት እባክህ ስጥ» በማለት በትህትና እንዲለምኑት መልዕክተኞች ይልክበታል። ናባል ግን ባለጌ ነበርና፡ - «ዳዊት ማነው? የእሴይስ ልጅ ማነው? እያንዳንዳቸው ከጌቶቻቸው የኮበለሉ ባሪያዎች ዛሬ ብዙዎች ናቸው።» በማለት ይመልሳል። የሰውን ልክ ባያውቅ ነው እንጂ ዳዊት፤ «ማን ነው?» የሚባል ሰው አልነበረም። በምዕ. 21፥10-11 ፍልስጥኤማውያን እንኳን

ሲመሰክሩለት እናነባለን፡፡ «ይህ ዳዊት የአገሩ ንጉሥ አይደለምን? ሳዖል ሺህ ዳዊትም እልፍ ገደለ ብለው ሴቶች በዘፈን የዘመሩለት እርሱ አይደለምን?»

እግዚአብሔር ቢያበለጽገን የእግዚአብሔርን ሕዝብና የተቸገሩትን እንድንረዳበት ነው እንጂ ለራሳችን ክብርና ድሎት አይደለም፡፡

ዳዊት የናባልን መልስ በሰማ ጊዜ ሰይፉን ታጥቆ አብረውት የነበሩትን 400 ሰዎችም ሰይፍአችሁን ታጠቁ ብሎ፣ ምናልባት «ማን እንደሆንኩ ላሳየው» በሚል መንፈስ ናባልንና ያሉትን ወንዶች ሁሉ ለማጥፋት ይነሣል፡፡

በዚህ መሀከል መንጋዎቹን ይጠብቁ ከነበሩት ብላቴናዎች አንዱ ስለ ዳዊት መልካምን ወሬ ለአቢግያ በመንገር የሆነውንና ሊሆን ያለውን ሁሉ ይነግራታል፡፡ እንደዚህ ዓይነት መልካም ወሬ የሚያወሩ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት ያስፈልጋሉ፡፡ ሐሜት ወይም የሐሰት ሙገሳ /ሽንገላ/ ሳይሆን እውነትን የሚያወሩና መፍትሔን የሚጠቁሙ ሰዎች የተባረኩ ናቸው፡፡ «... ከእነርሱ ጋር ሆነን መንጋውን በጠበቅንበት ዘመን ሁሉ ሌሊትና ቀን አጥር ሆነውን ነበር፡፡ ስለዚህም በጌታችንና በቤቱ ሁሉ ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ ተቈርጦአልና እርሱ ምናምንቴ ሰው ስለሆነ ማንም ሊናገረው አይችልምና የምታደርጊወን ተመልከቺና እወቂ፡፡»

አቢግያም ይህን በሰማች ጊዜ «<u>ፈጥና</u>» እርምጃ ስትወስድ እናያለን፡፡ አንዳንድ ሁኔታዎች ጊዜ የማይሰጡ ስለሆነ፣ ከዘገየን ነገር የሚበላሽበት፣ የሰው ነፍስ የሚጠፋበት ነገር ስለሆነ በፍጥነት ማድረግ አለብን፡፡ ዳዊትም፤ እጅ መንሻውን ይዛ በእግሩ ላይ ወድቃ በለመነችው ጊዜ፣ «እኔን ለመገናኘት <u>ፈጥነሽ</u> ባልመጣሽ ኖሮ እስኪነጋ ድረስ ለናባል አንድ ወንድ ስንኳ ባልቀረውም ነበር፡፡» ሲላት እንሰማለን፡፡

በአቢግያ ማስተዋል፣ ትኅትና፣ ፍጥነት ትጋት እና መስዋዕትነት ምክንያት የዚያ ሁሉ ሰው ደም ከጥፋት ሲተርፍ እናያለን፡፡

አቢግያ ወደ ዳዊት የቀረበችው የባልዋን የናባልን  ኃጢአት የራስዋ አድርጋ ነበር፡፡ «ጌታዬ ሆይ ይህ ኀጢአት በእኔ ላይ ይሁን» (ቁ. 24)፡፡ «የእኔን የባሪያህን ኀጢአት ይቅር በል ቁ. 28፡፡

አቢግያ ሊሞቱ ያላቸውን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ዳዊትንም በከንቱ ደም ከማፍሰስና ከኅሊና ጸጸት ለራሱም ከመበቀል ነበር ያዳናቸው፡፡ እንዲሁም «የእግዚአብሔርን ጦርነት ስለምትዋጋ» በማለት የራሱ ክብርና ስም ለምን ተነካ ብሎ እንዳይዋጋ ታሳስበዋለች፡፡ ዳዊት ምክርን የሚሰማ ሰው ስለነበረ «በደኅና ወደ ቤትሽ ሂጂ እነሆ፣ ቃልሽን ሰማሁ ፊትሽንም አከበርሁ» በማለት ያሰናብታታል፡፡»

እርስዋም ተመልሳ ስትሄድ ባልዋ ትልቅ ግብዣ አድርጎና ሰክሮ ደስም ብሎት ታገኘዋለች፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሞት በላያቸው እያንዣበበ፣ ቁጣ ወደ እነርሱ እየመጣ እንኳን ስለማያስተውሉ ሲፈነጥዙ እና በስንፍና ደስታ ውስጥ ሲዋኙ ይታያሉ፡፡ አቢግያም ስካሩ እስኪበርድለት ጠብቃ በማግሥቱ ሊሆን የነበረውን ነገር ሁሉ ስትነግረው «ልቡ በውስጡ ሞተ፣ እንደ ድንጋይም ሆነ፣ ከአሥር ቀንም በኋላ እግዚአብሔር ናባልን ቀሠፈው፣ እርሱም ሞተ፡፡»

እዚህ ላይ የምናያቸው ሁለት ነገሮች አሉ፤ አንደኛው፣ ቃል ምን ያህል ኀይለኛ እንደሆነ ነው፡፡ አቢግያ ሊሆን የነበረውን ነገር <u>ስትነግረው</u> «<u>ልቡ በውስጡ ሞተ</u>» ይላል፡፡ ቃል ሕይወትንም ሆነ ሞትን ያዘለ ሊሆን እንደሚችል እናያለን፡፡ «ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው» ምሳሌ 18÷21፡፡

ሁለተኛው የምናየው ነገር የእግዚአብሔርን ጻድቅ ፍርድ ነው ሊሞት የሚገባው ናባል ብቻ እንጂ ምንም ያላጠፉት ወንዶች ሁሉ መሞት ስላልነበረባቸው፣ እግዚአብሔር የዳዊትን ፍርድ ሽሮ የራሱን ቅን ፍርድ በራሱ ጊዜ ፈጸመ። የዳዊት ፍርድ ግን «ለእርሱም ከሆነው ሁሉ እስከነገ ጠዋት ድረስ አንድ ወንድ ስንኳ ብተው እግዚአብሔር በዳዊት ላይ እንዲህ ያድርግ እንዲህም ይጨምር» በማለት ነበር (ቁ. 22) የዳዊት ፍርድ ይዘቱም ሆነ ጊዜው የተዛባ ነበር።

## <u>ምዕራፍ ሃያ ስድስት</u>

በዚህም ምዕራፍ ዳዊት ሳዖልን እንደገና በጎሊና ውጊያ ሲያሸንፈው እናያለን፡-

ሳዖል እንደተለመደው ዳዊትን ለማሳደድ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ በአንድ ስፍራ በማረፍ ማታ ተኝተው ሳሉ፣ ዳዊት ሳዖል ወደሰፈረበት ሥፍራ በመሄድ የሳዖልን ጦርና የውሃ መቅጃውን ይዞበት ይሄዳል። «ከእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ እንቅልፍ ወድቆባቸው ነበርና ሁሉም ተኝተው ነበር እንጂ የነቃ አልነበረም።» ቁ. 12

በኋላም በተራራው ራስ ላይ ቆሞ የጦሩን መሪ አበኔርን «ጌታህን ንጉሡን የማትጠብቅ ስለምን ነው?» በማለት ይጠይቀዋል። ሳዖልም የዳዊትን ድምፅ ሲሰማ «በድያለሁ ስንፍና አድርጌአለሁ፣ <u>እጅግ ብዙም ስቻለሁ</u>።» በማለት ተጸጽቶ ይናገራል። በምዕ. 24 ላይ ዳዊት የሳዖልን ነፍስ ካዳነ በኋላ ሳዖል አልቅሶ ተጸጽቶ ነበረ፣ አሁን ደግሞ እንደገና ሲጸጸት እናያለን። ክፉ መንፈስ የሚነዳው ሰው ያ ክፉ መንፈስ በሚነዳው መንገድ እንጂ በራሱ ስሜትና ኀሊና እንኳን መሄድ አይችልም።

በመጨረሻም ሳዖል ዳዊትን «ልጄ ዳዊት ሆይ፣ ብሩክ ሁን ማድረግን ታደርጋለህ፣ መቻልንም ትችላለህ» ሲለው እናነባለን። ነገር ግን ዳዊት ያደረገውና የቻለው እግዚአብሔር ስላስቻለው ነበር።

ብርቱ ብርቱ ብርቱ ነው
እግዚአብሔር እርሱ ብርቱ ነው
ሁሉን ችሎ ሁሉን የሚያስችለው
እግዚአብሔር ብርቱ ነው

እግዚአብሔር ከባድን እንቅልፍ በሳዖልና በሠራዊቱ ላይ ባያመጣ ኖሮ ዳዊት ያደረገውን ማድረግ ባልቻለም ነበር።

## <u>ምዕራፍ ሃያ ሰባት</u>

በዚህ ምዕራፍ ዳዊት ከሳዖል ስደት ለማረፍ ብሎ ወደ ፍልስጥኤማውያን ንጉሥ ሲሸሽ እናያለን ከዚህ የምንማረው፤ በእግዚአብሔር ቤት በሚነግሠው ጦርነት ምክንያት ስንት ሰዎች ከእግዚአብሔር ቤትና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለመራቅ ተገድደው ወደ ጠላት ሠፈር እንደሚሄዱ ነው፤ አንዳንድ ጨቅላ የሆኑ አማኞች እስከ መሰናከልና በጠላት እስከ መወሰድ ይደርሳሉ።

ዳዊት ግን በአምላኩ ላይ የጸና እምነት ስለነበረው፣ ወደ ጠላት ሠፈር ለመሰደድ ቢገደድም የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ አንኩስ የጺግላግን ከተማ ሰጥቶት ስለነበር ጺቅላግ እስከ ዛሬ ድረስ ለይሁዳ ነገሥታት ሆነች።» ቁ. 6 የሚል ምስክርነት ተጽፎለት እናነባለን። አምላኩን የሚያውቅ ሰው በስደት ሆኖ እንኳን የጠላትን ከተማ ይማርካል።

ምዕ. 28፡ - ዳዊት ወደ ፍልስጥኤማውያን ንጉሥ ከተጠጋ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤላዊያን ጋር ለመዋጋት ሲሰለፉ፣ የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ አንኩስም ዳዊትን፡ - «አንተና ሰዎችህ ከእኔ ጋር ወደ ሰልፍ እንድትወጡ በእርግጥ እወቅ አለው።» ዳዊትም የአዎንታ መልስ በመስጠት ከእርሱ ጋር አብሮ እንደሚዋጋ ያረጋግጥለታል። ይህ በጣም የሚያሳዝን ሁኔታ ነው። የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ሐሳብን በምናይበት ጊዜ ዳዊትም ሆነ ሳዖል በእስራኤል ላይ የተቀበሉበት አንዱ ዓላማ የእስራኤላዊያንን ጠላት፣ በተለይ ፍልስጥኤማውያንን ለመዋጋት ነበር። ነገር ግን በሳዖል ከእግዚአብሔር ፈቃድ መውጣት ምክንያት ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር አብሮ ተሰልፎ እስራኤልን ለመውጋት ሲገደድ እናያለን። በምዕ. 29 እንደምናየው እግዚአብሔር በምሕረቱ መንገዱን ባይዘጋበት ኖሮ ምናልባት የራሱን ወገን ሳይወጋ አይቀርም ነበር።

ከቁ. 3-25 ድረስ ባለው ክፍል የምናየው ሳዖል ሰልፉን ባየ ጊዜ በጣም ስለፈራና ስለተንቀጠቀጠ፣ እግዚአብሔርንም ቢጠይቅ ምንም መልስ ስላላገኘ፤ እራሱ አውግዞና እንዲጠፉ አውጆ ቢሆንም፤ ወደ አንዲት ጠንቋይ ራሱን ሰውሮ ሲሄድ እናያለን።

ከዚህ የምንማረው፤

1ኛ እግዚአብሔር የኃጢአተኞችን ጸሎት እንደማይሰማ ነው። እግዚአብሔር ከኃጢአተኞች መስማት የሚፈልገው ጸሎት የንሥሐ ጸሎት ብቻ ነው። ሌላ ማንኛውንም ጸሎት ግን አይሰማም።
2ኛ አንድ፣ እራሱ በአመጽ ውስጥ ያለ ሰው ሌሎችን ስለ አመጻቸው ማውገዝ ግብዝነት እንደሆነ።

ሳዖል፣ እራሱ በአመጽ ውስጥ ሆኖ፤ «ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፣ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው» (1ሳሙ. 15÷23) ተብሎ ራሱ ከተወገዘ በኋላ የራሱን አመጽና ዳዊትን ማሳደዱን ሳይተው በአገሪቱ የነበሩትን ምዋርተኞችንና ጠንቋዮችን ሁሉ አውግዞና አጥፍቶ እንደነበረ እናነባለን። (ቁ. 3) ጭንቀት ሲይዘው ግን ራሱ ወዳጠፋቸው ጠ ንቋዮች በመሄድ አንዷን መናፍስት ጠሪ «ሳሙኤልን አስነሽልኝ» ብሎ ሲጠይቃት እናያለን (ቁ. 8-11)።

ይህ የሳዖል ጥያቄ በዘዳ. 18÷11 ላይ በእግዚአብሔር የተወገዘ ድርጊት እንደነበረ እናያለን። ሳዖል ሳሙኤልን እንድታስነሣለት ያቺን መናፍስት የምትጠራ ሴት በጠየቃት ጊዜ እርስዋንም እንኳን ያስደነገጣት ነገር እንዳየች እናነባለን። ለወትሮው የምታደርገው ዓይነት መናፍስትን መጥራት ቢሆን ኖሮ የተለማመደችው ሥራዋ ነውና ባልጮኸችም ነበር። ነገር ግን በዚህ ትእይንት ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ ጣልቃ የገባ ይመስላል። እርሱ የጌቶች ጌታ፣ የአማልክት አምላክ የኃይላት ሁሉ ኃያል ነውና ለሳዖል የመጨረሻውን መርዶና የአመጹን ፍጻሜ ሊነግረው ነቢዩ ሳሙኤል እንዲገለጽ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ። ሰይጣን በራሱ ኃይል የሞተን ሰው መንፈስ ከሙታን ማስነሣት ሥልጣን አልተሰጠውም። መናፍስት ራሳቸውን በሞቱ ሰዎች መልክ አድርገው እንደሚያቀርቡ ግልጽ ነው። በዚህ ክፍል ግን የሰይጣን መሣሪያ የነበረችውን ሴት እንኳን ያስደነገጠ ትእይንት ሲከናወንና ነቢዩ ሳሙኤል ግልጽ የሆነና በነጋታው የሚፈጸም ትንቢት ሲነግረው እናነባለን ከቁ. 15-19 ያለውን የሳሙኤልን ቃል ስናነብ ሳሙኤል በምድር ሆኖ ይናገር እንደነበረው አንዲት እንኳን መሬት የማትወድቅ ነገር ሲናገር እንሰማለን። «ሳሙኤልም አለ፡- እግዚአብሔር ከራቀህ ጠላትም ከሆነህ ለምን ትጠይቀኛለህ? እግዚአብሔር በቃሌ እንደ ተናገረ አድርጓል እግዚአብሔርም መንግሥትህን ከእጅህ ነጥቆ ለጎረቤትህ ለዳዊት ሰጥቶታል የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማህምና በአማሌቅም ላይ ታላቅ የሆነ ቁጣውን ኣላደረግህም ስለዚህ ዛሬ እግዚአብሔር በቃሌ እንደ ተናገረ አድርጓል እግዚአብሔርም መንግሥትህን ከእጅህ ነጥቆ ለጎረቤትህ ለዳዊት ሰጥቶታል የእግዚአብሔርን

ቃል አልሰማህምና በአማሌቅም ላይ ታላቅ የሆነ ቁጣውን አላደረግህምና ስለዚህ ዛሬ እግዚአብሔር ይህን ነገር አድርጎብሃል። ... ነገም አንተና ልጆችህ ከእኔ ጋር ትሆናላችሁ።» ይህ ክፍል ትንሽ አሻሚና አከራካሪ ክፍል ስለሆነ ምናልባት አንዳንድ ጥያቄዎችን ብንጠይቅ የበለጠ ግልጽ ይሆንልናል። የተነሣው መንፈስ ሳሙኤል ሳይሆን ሳሙኤን ተመስሎ የመጣ ርኩስ መንፈስ ከሆነ፣ ያቺ ሴት ይህንን በተለምዶ የምታደርገውን ነገር ስታይ ለምን በታላቅ ድምፅ ጮኸች? ነገር ግን ነቢዩ ሳሙኤል በየቦታው በመናፍስት ጠሪዋ ሥልጣን ሳይሆን በእግዚአብሔር ሥልጣንና ፈቃድ የእግዚአብሔርን ግርማ ለብሶ እንደተነሣ እናያለን። ይህም ነገር እርስዋ ከዚህ በፊት ከተለማመደችው ሥልጣንና ልምምድ በላይ ስለሆነባት በታላቅ ድምፅ ጮኸች። በሳሙኤል የነበረው የእውነት መንፈስ ተሰውሮና መልኩን ለውጦ የመጣው ሰው ሳዖል መሆኑን ሲገልጥ እናያለን። ሌላ መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ሰይጣን የውሸት አባት እንደመሆኑና የወደፊቱን ሁሉ ማወቅ የማይችል እንደመሆኑ መጠን በሳሙኤል ተመስሎ የተናገረው እርሱ ወይም ርኩስ መንፈስ ከሆነ ትንሽ ውሸት ወይም ስህተት የሆነ ነገር በተደባለቀበት ነበር። ነገር ግን ሳሙኤል ተነሥቶ የተናገረው ሁሉ እውነትና በትክክል የተፈጸመ ነገር እንደነበረ እናያለን። እግዚአብሔር በዚህች መናፍስት ጠሪ አማካይነት (በእርስዋ ውስጥ በሚሠራው መንፈስ ሥልጣን ሳይሆን) ነቢዩ ሳሙኤል እንዲነሣና ለሳዖል የትንቢትን ቃል እንዲናገር መፍቀዱ፣ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነትና በመናፍስት አለም እንኳን እግዚአብሔር እንደሚሰለጥን ያሳያል። እግዚአብሔር በዚህች መናፍስት ጠሪ በኩል ይህ እርስዋንም እንኳ ያስደነገጠ ነገር እንዲሆን መፍቀዱ፣ ቀደም ሲል በዘኍ 23 ና 24 ላይ መተተኛ ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተጠራው በሐሰተኛው ነቢይ በበለዓም እንኳን የበረከትን ቃል ለእስራኤል ሲያስተላልፍ ካየነው ጋር ተመሳሳይነት አለው። እግዚአብሔር በፈቀደው መንገድ ፈቃዱንና መልእክቱን ማስተላለፍ ይችላል። ሰይጣንንም እንኳን ሳያውቅ እግዚአብሔርን ሐሳብ እንዲፈጽም ያደርገዋል።

«ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳን ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር።» 1ቆሮ. 2፥8

## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ለመዋጋት ለሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ ዳዊትም ከንጉሥ አንኩስ ጋር ወገኖቹን (እስራኤላውያንን) ለመዋጋት አብሮ ለሰልፍ ሲወጣ እናያለን። በዚህ ምዕራፍ እንደ ዳዊት ሐሳብ ቢሆን ኖሮ የገዛ ወገኖቹን ደም ባፈሰሰ ነበር። ወደዚህ ሰልፍ የወጣውም ንጉሥ አንኩስ «ከእኔ ጋር ወደ ሰልፍ እንድትወጡ በእርግጥ እወቅ።» (ምዕ. 28፥1) ስላለው እንጂ እንደ ልማዱ እግዚአብሔርን ጠይቆ አልነበረም። እግዚአብሔር ግን በምሕረቱ የገዛ ወገኖቹን ደም እንዳያፈስ ሲጠብቀው እናያለን። የፍልስጥኤማውያን አለቆች «እነዚህ ዕብራውያን በዚህ ምን ያደርጋሉ?» ብለው ስለጠየቁና ስለተቃወሙ ዳዊት ከሰልፉ ሲቀር እናያለን። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የእርሱ ፈቃድ ካልሆነ ነገር ውስጥ በምሕረቱ አውጥቶን እንኳን የማንረዳበት ጊዜ አለ።

## ምዕራፍ ሠላሳ

በዚህ ምዕራፍ ዳዊት ከሰልፉ ከተመለሰ በኋላ ወደሚኖርበት ወደ ጺቅላግ ከተማ ሲደርስ አማሌቃውያን ከተማዋን አቃጥለዋትና ዘርፈዋት፣ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ሁሉ ማርከው እንደሄዱ ከቁ. 1-6 እናነባለን። «ዳዊት፣ ከእርሱም ጋር የነበሩ ሕዝብ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለማልቀስ ኃይል እስኪያጡ ድረስ አለቀሱ።» (ቁ. 4)

«ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች ልጆቻቸው የሕዝቡ ልብ ተቆጥቶ ነበርና ሕዝቡ ሊወግሩት ስለተናገሩ ዳዊት እጅግ ተጨነቀ፤ <u>ዳዊት ግን በአምላኩ በእግዚአብሔር ልቡን አበረታ</u>።» ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳንጠይቅ የምንወስደው እርምጃ ሁሉ ለጠላት እንደሚመችና ለጠላት የተጋለጥን እንደሚያደርገን ነው። ዳዊት ከጅምሩ አምላኩን ቢጠይቅ ኖሮ «አርፈህ ተቀመጥ» ይለው ነበር። ከዚህ ጭንቀትና መከራም ይተርፍ ነበር። «የሚሰማኝ ግን በርጋታ ይቀመጣል ከመከራም ሥጋት ያርፋል።» (ምሳሌ 1፥33)

ዳዊት ምንም ቢሳሳት አምላኩን በግል የሚያውቅ ሰው ስለነበረ፣ የገዛ ራሱ ሕዝብ ሊወግሩት በነበረ ጊዜ «ዳዊት ግን በአምላኩ በእግዚአብሔር ልቡን አበረታ» ይላል። ይህ ቃል ትልቅ ሚስጥርን ያዘለ ቃል ነው። በአካባቢያችን ያሉት ሁሉ፤ የእኔ የምንላቸው እንኳን ሳይቀሩ ጠላቶች ቢሆኑብን፣ አይዞህ የሚልህ የሚያጽናና ባይኖር፣ እኛ በእግዚአብሔር ከታመንንና እርሱን የሙጥኝ ካልን እርሱ ብቻ ይበቃናል። በእርሱ ልባችንን ማበርታት እንችላለን። «እግዚአብሔር ከእኛ (ከእኔ) ጋር ከሆነ (ማን ይቃወመናል) ማን ይቃወመኛል ? ሮሜ 8፥31 እግዚአብሔር የግል አምላክ እንጂ የጅምላ አምላክ አይደለም። በዳን 11፥32 ላይ እንዲህ ይላል፤ «ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ ያደርጋሉም።»

ዳዊት ልቡን በእግዚአብሔር ካበረታ በኋላ ካህኑን አብያታርን ኤፉዱን አቅርብልኝ ብሎ እግዚአብሔርን በቀጥታ ይጠይቀዋል፡- «የእነዚህን ሠራዊት ፈለግ ተከትዬ ልሂድን» አገኛቸዋለሁን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ።» (ቁ. 8) እግዚአብሔርም «ታገኛቸዋለህና፣ ፈጽመህም ምርኮውን ትመልሳለህና ፈለጋቸውን ተከተል ብሎ መለሰለት። አምላኩን በግል የሚያውቅ ሰው ቢሳሳትና ጠላት ምርኮ ቢወስድበት እንኳን ተስፋ አይቆርጥም። በአምላኩ ፊት በመቅረብ መጽናናትንና ኃይልን ከተቀበለ በኋላ የአምላኩን ምሪት ሰምቶ ምርኮውን ማስመለስ ብቻ ሳይሆን ጠላቱን ያደባያል፣ ተጨማሪ የጠላትን ምርኮ በዝብዞ ይመለሳል። ዳዊት በእግዚአብሐር ምሪትና እርዳታ ይህንን ነበረ ያደረገው።

«ዳዊትም አማሌቃውያን የወሰዱትን ሁሉ አስጣላቸው፣ ሁለቱንም ሚስቶቹን አዳነ። ... ከወሰዱትም ምርኮ ምንም የጎደለባቸው የለም፤ ዳዊትም ሁሉን አስጣለ። የበጉንና የላሙን መንጋ ሁሉ ወሰደ ከራሱም ከብት ፊት እየነዳ ይህ የዳዊት ምርኮ ነው አለ።» (ቁ 18-20)

ከቁ. 11-16፡ - የእግዚአብሔርን እርዳታ እናያለን። እግዚአብሔር ምርኮአችንን እንድናስመልስ በመንገዳችን ላይ የሚያዘጋጃቸው ጠቋሚዎች አሉ። አማሌቃውያን ጺቅላግን በዝብዘውና በእሳት አቃጥለው ከተመለሱ በኋላ አንድ ግብጻዊ ባሪያ ሲታመምባቸው በበረሃ ውስጥ ጥለውት ይሄዳሉ። ይህንን ሰው ዳዊት በመንገድ ላይ ያገኘውና፣ ደክሞና በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ስለነበረ ካጠጡትና ካበሉት በኋላ ማንነቱን ሲጠይቁት የአማሌቃውያን ባሪያ እንደሆነ ይነግራቸዋል። በዚህ ሰው ምሪት አማሌቃውያን ወዳሉበት ሰፈር መድረስ ይችላሉ።

ዳዊት አማሌቃውያንን መትቶ ምርኮን ከማረከ በኋላ አብረውት አማሌቃውያንን ለተዋጉትና ደክመው ስለነበር በባሦር ወንዝ ማዶ በመሆን ዕቃ ይጠብቁ ለነበሩት እኩል ምርኮውን ሲያካፍላቸው እናያለን። «ዳዊትም ወንድሞቼ ሆይ የጠበቀን በእኛም ላይ የመጣውን ጭፍራ በእጃችን አሳልፎ የሰጠን እግዚአብሔር በሰጠን ነገር እንዲህ አታድርጉ፣ ይህንስ ነገር ማን ይሰማችኋል? ነገር ግን የተዋጉትና ዕቃውን የጠበቁት እድል ፈንታ እኩል ይሆናል፣ አንድነት ይካፈላሉ አለ» (ቁ. 23-24)። ዳዊት ይህን የመለሰላቸው ከተዋጉት መካከል አንዳንዶቹ ምርኮውን ላልተዋጉት አናካፍልም ስላሉ ነበር። አንዳንድ ጊዜ እኛም እግዚአብሔር በሰጠን ኃይልና ጸጋ ባደረግነው ነገር ተመክተን ሌሎችን ወደታች የምናይበት ጊዜ አለ። «የሚያገለግልም ቢሆን እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የታዘዛችሁትን ከፈጸማችሁ በኋላ «እኛ የማንጠቅም ባሪያዎች የሚገባንን አደረግን» በሉ ተባልን እንጂ በሌሎች ድካም

ላይ ፍረዱና ተመኩ አልተባልንም፡፡ አንዱ ብልት ሲከብር ብልቶች ሁሉ እኩል ደስ ሊላቸው ይገባል፡፡ የአንዳችን ድል የሁላችንም ደስታ መሆን አለበት፡፡

ዳዊት ለተዋጉትና ዕቃውን ይጠብቁ ለነበሩት ብቻ ሳይሆን በይሁዳ ለነበሩ ስለ ውጊያው እንኳን ለማያውቁ ወገኖቹ ከምርኮው ሲልክላቸው እናያለን፡፡ «ዳዊትም ወደ ጺቅላግ በመጣ ጊዜ ለዘመዶቹ ለይሁዳ ሽማግሌዎች እነሆ ከእግዚአብሔር ጠላቶች ምርኮ በረከትን ተቀበሉ ብሎ ከምርኮው ሰደደላቸው፡፡ በቤቴል ለነበሩ፣ በራሞት ደቡብ ለነበሩ ... በኬብሮን ለነበሩ፣ ዳዊትና ሰዎቹም በተመላለሱበት ሥፍራ ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ላከ፡፡» ዳዊት የመስጠትና የማካፈል ምስጢር የገባው የእግዚአብሔር ሰው ነበረ፡፡

## <u>ምዕራፍ ሰላሳ አንድ</u>

እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ፊት እንደሸሹና ተሸንፈው እንደወደቁ፤ እንዲሁም ሳዖልና ልጆቹ ሁሉ እንደሞቱ የሚያሳይ ምዕራፍ ነው፡፡ ሳዖል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሆኖ የነበረበትን የአመጽ ዘመን ሁሉ ውጤት ሲያጭድ እናያለን፡፡ በመጨረሻ ላይ በራሱ ሰይፍ ላይ ወድቆ ራሱን ይገድላል፡፡ ዳዊት በምዕ. 17 ላይ በአምላኩ ታምኖ ጎልያድን በመግደል የጎልያድን ራስ ቆርጦ የጎልያድን የጦር ዕቃ እንደወሰደና የጎልያድ ሰይፍ በእግዚአብሔር ቤት እንደነበር በምዕ. 21÷9 ላይ እናያለን፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ አምጾ የነበረው ሳዖል ራሱ በጠላት ተቆርጦ መዘበቻ ሲሆንና የጦር ዕቃው ደግሞ በአስታሮት መቅደስ ሲቀመጥ እናያለን፡፡ አንዱ እግዚአብሔርን ሲያከብርና ሲያስከብር ሌላው ግን የእግዚአብሔርን ነገር ስለናቀ ሲዋረድና የእግዚብሔርንም ስም ሲያሰድብ እናያለን፡፡ እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን» (1ጴጥ. 4÷11)፡፡


*Global Good News Literature*

*P.O.Box 451336*

*Los Angeles, CA 90045*


(C) Copyright 2013